የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

የገቢ ሂሳብ፣

1. የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ከደመወዝ ጋር ተደምሮ መቀነስ የነበረበት በአጠቅላይ ብር 3,542,798.36 የሥራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡
2. ከተለያዩ አቅራቢ ድርጅቶች መከፈል የነበረበት የጉዳት ካሳ ብር 334,650.15 ተቀንሶ ገቢ አለመደረጉን በኦዲት ተረጋግጧል::

የወጪ ሂሳብ፣

3. ዩኒቨርሲቲው በተፈቀደው መሰረት መክፈል ሲገባው፣ ሥራ ላይ ለሌሉ መምህራን በአጠቃላይ ብር 1,848,000.00 የትራንስፖርት አበል ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
4. በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ በድምሩ ብር 2,112,407.70 የቤት አበል ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
5. ትምህርታቸውን ያቋረጡ ወይም ያራዘሙ መምህራን ከሚማሩበት ተቋም ያቋረጡበትን ወይም ያራዘሙበትን ምክንያት የሚገልፅ የፅሁፍ ማስረጃ ሳያቀርቡ ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ሥራ ገበታቸው የሚመለሱበት ጊዜ ያለፈባቸው መምህራን ትምህርት ላይ እንዳሉ ተደርጎ የቤት አበል፣ የትራንስፖርት አበልና ደመወዝ በድምሩ ብር 802,291.00 አለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

6. በደቡብ አፍሪካ የሚማሩ አንድ የዩኒቨርሲቲው መምህር በመመሪያው መሰረት በየወሩ ግማሽ ደመወዝ መከፈል ሲገባው፣ ሙሉ ደመውዝ በመክፈል ከሐምሌ 2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 2009 ዓ.ም በልዩነት ብር 62,139.00 ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
7. ዩኒቨርሲቲው ለሚመለከተው አካል ሳያስፈቅድ ወይም ደንብና መመሪያን መሰረት ያላደረገ በራሱ የክፍያ ስርዓት አውጥቶ በአጠቃላይ ብር **3,445,890.10** የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ያለአግባብ ክፍያ የፈጸመ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡
8. ዩኒቨርሲቲው ከደንብና መመሪያ ውጭ በመንግስት በጀት ለሚተዳደሩ ተቋማት ድጋፍ በሚል በድምሩ ብር **1,044,153.92** ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
9. በአጠቃላይ ብር **31,556,591.59** በመመሪያው መሰረት የመያዣ ሂሳብ ቋት እና ተቀጽላ ቋት ተከፍቶለት በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡
10. በድምሩ ብር **932,570.54** ዝቅተኛ ዋጋ አቅራቢ ድርጅት እያለ ከፍተኛ ዋጋ አቅራቢ ከሆነው በመገዛቱ መንግስት ማግኘት የሚገባውን ገንዘብ እንዲያጣ መደረጉን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡
11. ዩኒቨርሲቲው በአዋጁ መሰረት አገልግሎቱ ከአንድ አቅራቢ ብቻ የሚገኝ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ሳያቀርብ እና የመንግስት ሀብት ቆጣቢ በሆነ መልክ ግዥውን ማከናወን ሲገባው፣ በድምሩ ብር **2,929,792.85** በቀጥታ ግዥ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
12. ዩኒቨርሲቲው ብዙ አቅራቢዎች መኖሩን እያወቀ ወይም ውስን አቅራቢ ስለመሆናቸው ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ሳይቀርብ በብር **527,745.14** የመጋረጃ ግዥ ከአንድ የጨርቃ ጨርቅ መደብር በውስን ጨረታ ግዥ የፈጸመ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
13. ዩኒቨርሲቲው የግዥ ፍላጎትን አሰባስቦ ግዥ መፈጸም ሲገባው፣ በድምሩ ብር 3,703,185.24 ቆራርጦ በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ የፈጸመ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
14. ዩኒቨርሲቲው በመመሪያው መሰረት ክፍያ ማከናወን ሲገባው፣ መከፈል ከነበረበት በላይ በድምሩ ብር 177,073.00 በልዩነት ያለአግባብ የውሎ አበል ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

<u>የተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

15. ዩኒቨርሲቲው በተለያዩ የሂሳብ መደቦች ከ2003 ዓ.ም እስከ 2009 ዓም በተሰብሳቢ የተየዙ ሂሳቦች በድምሩ ብር 34,778,778.90 በደንቡና በመመሪያው መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ መገኘቱን ተረጋግጧል፡፡

<u>የተከፋይ ሂሳብ፣</u>

16. ለተለያዩ ድርጅቶችና ግለሰቦች የሚከፈል ሂሳብ ብር 68,875.26 ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2009 ዓ.ም በዕዳነት የተያዘ ሂሳብ በወቅቱ ሳይወራረድ መገኘቱን ተረጋግጧል፡፡

በጀት፣

17.ዩኒቨርሲቲው ለመደበኛ በጀት ብር 776,111.60 ከተፈቀደው በጀት በላይ የተጠቀመ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 17 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርስቲውው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

- ዩኒቨርሲቲው በመመሪያው መሰረት በግቢ ውስጥ ለሚያስገነባቸው የተለያዩ የግንባታ ስራዎች ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊነት ሊወስድ የሚችል የአማካሪነት ፍቃድ ባለው አማካሪ ድርጅት ቀጥሮ ማሰራት ሲገባው በድምሩ ብር **71,295,914.67** በዩኒቨርሲቲው የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በአማካሪነት እና የክፍያ ሰርተፊኬት እንደሚያዘጋጅ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡
- ዩኒቨርሲቲው የላቦራቶሪ ዕቃዎች እና የህትመት ማሽን ለመግዛት ከ2006 ዓ.ም እስከ 2009 ዓ.ም የሌተር ኦፍ ክሬዲት /letter of Credit/ በዓለም አቀፍ ስምምነት በባንክ በኩል ለገባው ዋስትና የሚተላለፈውን ገንዘብ ለዚህ ተብሎ ለተያዘው በሂሳብ መደብ 4104 መመዝገብ ሲገባው፣ ለዕቃ አቅራቢዎች የሚፈጸም የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የሚመዘገብበት በሂሳብ መደብ 4253 ብር **18,297,434.93** የተያዘ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
- በድምሩ ብር **4,400,406.55** የተገዙ ዕቃዎች በናሙናው መሰረት ገቢ ስለመሆናቸው የቴክኒክ ኮሚቴ ያረጋገጠበት ደብዳቤ ከክፍያ ሰነድ ጋር ያልተያያዘ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
- በድምሩ ብር **3,194,400.09** የሂሳብ መደቡን ባልጠበቀ ሁኔታ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- በልዩ ልዩ የወጪ ሂሳብ መደቦች ውስጥ ያልተሰራበት ከመደበኛ በጀት ብር 166,180,563.72 እና ከካፒታል በጀት ብር 181,300,933.51 በድምሩ ብር 347,481,497.23 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች፣

- የተሸከርካሪ የመለዋወጫ ዕቃዎች ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ እንዲሁም የንብረት ወጪ የሚሰራ በአንድ ሰዉ መሆኑን፣

- የሚወገዱ የተለያዩ የመኪና ጎማዎች ብዛት 250፣ የመኪና ባትሪዎች ብዛት 83፣ ከመነዳሪያ ብዛት 80፣ ፍላፓ በቁጥር 150 እና የተለያዩ አሮጌ ሞተር ሳይክሎች በቁጥር 6 የሚሆኑ መወገድ ሲገባ ንብረት ክፍል ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑን፣
- አገልግሎት የማይሰጡ ወይም በብልሽት ምክንያት የቆሙ ተሽርከሪዎች ተጠግነው አገልግሎት የሚሰጡ ከሆነ ተጣርተው መጠገን ሲገባው ወይም መወገድ ካለባቸው ሳይወገዱ ሰሌዳ ቁጥር 4-03511 ቶዮታ ፒካፕ፣ ሰሌዳ ቁ 4-07079 IVCO፣ ሰሌዳ ቁጥር 4-01232 ቶዮታ፣ ሰሌደ ቁጥር 4-03515 ቶዮታ እና 4-01698 ኒሳን ፒካፕ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ያለአገልግሎት የቆሙ መሆኑን፣
- በዓለም አቀፍ ጨረታ የተገዙ ብዛት ያላቸው የቅየሳ (ሰርቬይንግ) መሳሪያዎች የተቀመጠውን የናሙና መስፈርት ባለማሟላታቸው በሚል ጉዳዩ ተጣርቶ የቴክኒክ መስፈርቱን ካላሟላ ለአቅራቢው ተመላሽ ማድረግ ወይም የናሙናው ትክክለኝነት ተጣርቶ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ሆኖ አገልግሎት መስጠት ሲገባው ከሁለት ዓመት በላይ ሞ/19 ሳይቆረጥለት በቋሚ ንብረት ክፍል ውስጥ ያለ አገልግሎት የሚቀመጥ መሆኑን ተረጋግጧል።
- የ2009 በጀት ዓመት ንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም የቆጠራ ውጤት ሪፖርት ተጠናቆ ያልቀረበ መሆኑን፣
- በ2008 በጀት ዓመቱ የተገዙ የተለያዩ የአላቂ ዕቃዎች በወቅቱ ለተጠቃሚዎች ተሰጥተው አገልግሎት ላይ መዋል ሲገባው በዋና ንብረት ክፍልና በሚኒ ንብረት ክፍል ውስጥ ጥቅም ላይ ሳይውሉ ወደ 2009 በጀት ዓመት የዞሩ ቢሆንም፣ ያለው ስራ ላይ ሳይውል በተጨማሪ ተመሳሳይ ግዥ በመፈጸም ያለአስፈላጊ ወጪ ከማስከተሉም በተጨማሪ የንብረት ክፍል ጥበት ያስከተለ መሆኑን፣
- የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃ እና አላቂ የጽዳት ዕቃ ክፍል ቢን ካርድ፤ ስቶክ ካርድ እና ንብረት ወጪ በአንድ ሰዉ የሚሰራ መሆኑን፣
- የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃ ክፍል ውስጥ አገልግሎት የማይሰጥ ፍሪጅ መወገድ ካለበት ሳይወገድ ወይም ተጠግኖ አገልግሎት መስጠት ሳይችል ከአንድ ዓመት በላይ የተቀመጠ መሆኑን፣
- የውሃና የመብራት የጥገና ግብአቶች ቢን ካርድ እና ስቶር ካርድ የተወሰነ መጠቀም የጀመሩ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ ያልተገባ መሆኑን፣
- የውሃና የመብራት የጥገና ግብአቶች ተለዋዋጭ አላቂ ዕቃዎች ተመላሽ የሚሆኑበት ስርዓት የሌለና ተመላሽ ዕቃዎች ገቢ የማይደረጉ መሆኑን፣

- የእንጨት ምርትና ጥገና ክፍልን ግብአቶች ንብረት የወጪ ሰነድ ሞዴል 22 እንዲሁም እስቶክ ካርድና ቢን ካርድ በአንድ ሰው የሚሰራ መሆኑን፣
- የተበላሹ ግራይንደሮች፣ ድሪሎች፣ ሮተሮች፣ ሳንደሮች እና የብረት መቁረጫዎች ጥገና ሳይደረግላቸው ለረጅም ጊዜ ያለመፍትሄ የተቀመጡ መሆናቸው፡፡
- ከጥቅም ውጭ የሆኑና መወገድ ያለባቸው ብዛት ያላቸው የተገነጣጠሉ በሮች፤የተሰባበሩ ሼልፎች እና ብረታ ብረቶች ተከማችተው የእንጨት ምርትና ጥገና ክፍል ፊት ለፊት የሚገኝ መሆኑን፣ ተረጋግጧል፡፡

<u>በ2008 ኦዲት ግኝቶች ላይ ስለተወሰደ የእርምት እርምጃ፣</u>

- የቤት አበል ላይ የቤት ተመን ዋጋ እየተቀነሰ ልዩነቱ የቤት አበል በሚል በድምሩ 162,650.00 ብር ያላግባብ ተከፈላቸው ተገኝቷል፡፡
- በውጭ ሀገር ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ መምህራን መመለስ በነበረባቸው ሳይመለሱ የቆዩ በድምሩ ብር 40,442.00 ያለአግባብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- በጠቅላላ ብር 1,035,900.00 ዩኒቨርሲቲው በራሱ የክፍያ ስርዓት በማውጣት ከመደበኛ በጀት ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- ዩኒቨርስቲ ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች ለጥናትና ምርምር ማካሄጃ (Msc Thesis) ድጎማ አዲስ የሚገቡ ተማሪዎችን ለመፈተን ወደ ተለያዩ ክልሎች ለተንዓዙ መምህራን የሞያ አበል እና ካሪኩለም ሪቪዉ ወርክ ሾፕ (curriculum review work shop) ላይ ለተሳተፉ በሚል ብር 772,610.00 አላግባብ ከመንግስት መመሪያና ደንብ ውጪ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱን፣
- በድምሩ ብር 1,777,374.15 የተለየያዩ ዕቃዎች በዋጋ ማቅረቢያ የተገዛ መሆኑን፣
- በጠቅላላ የብር 4,209,386.47 በግልፅ በጨረታ መገዛት ሲገባው በቀጥታ የተፈጸመ መሆኑ፣
- የብር 7,296,089.99 ወጪዎች የሂሳብ መደባቸውን መሰረት ያላደረገ መሆኑ፣
- በድምር ብር 913,544.48 በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ክፍያ መፈፀሙ ተረጋግጧል፡፡
- ዩኒቨርሲቲው ለአንድ ኮንትራክተርና ለአንድ አማካሪ ድርጅት በጠቅላላ ብር 28,906,495.29 ከመመሪያው ውጭ ከጠቅላላ ዋጋ ከ30% በላይ ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- በጠቅላላ ብር 39,697,017.64 ባላላቀ ስራ ከውሉ በላይ በብልጫ ተከፈሎ ተገኝቷል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

መግቢያ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፣

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፣

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት ያደረገው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ /የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል፡፡

አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ሲሆን የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የዩኒቨርሲቲው የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. <u>የገቢ ሂሳብ</u>፣

1.1.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>ከተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች መቀነስ የነበረበት የሥራ ግብር</u>፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በ07 ጥር 2005 በቁጥር 6.4.0/637/22 በተፃፈ ደብዳቤ ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች ለቤት ኪራይ ድጋፍ፣ ለፎቶ ኮፒ፤ ለፅህፈት መሣሪያ ግዥ ድጋፍ፣ የትራንስፖርት አበል ድጋፍ እና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚፈፀሙ ክፍያዎች በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ.3 ከፊደል "ሀ" እስከ "ሸ" ተዘርዝረው ነፃ ከተደረጉት ውስጥ የማይካታቱ በመሆናቸው ግብር የሚከፈልባቸው መሆኑን አሳውቋል፡፡ በተጨማሪም የመንግስት መ/ቤቶችና ልማት ድርጅቶች እንዲሁም ሌሎች ድርጅቶችና ተቋማት ከተቀጣሪዎቻቸው ሊቀንሱት የሚገባውን የሥራ ግብርን በተመለከተ በቁጥር 1 አውግ-54/ በ9 ነሐሴ 2000 በተፃፈ ደብደቤ በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 ከግብር ነፃ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማናቸውም ክፍያ ወይም ጥቅም ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት ባለስልጣን መ/ቤቱ ገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፡-

- ለመምህራንና ኃላፊዎች የትራንስፖርት አበል እየከፈላቸው ቢሆንም፣ የሚከፈላቸው ጥቅማ ጥቅሞች ከደመወዝ ጋር ተደምሮ የሥራ ግብር መቀነስ ሲገባው ከሐምሌ 2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ከተከፈላቸው ደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞች በአጠቃላይ ብር **3,185,736.15** የሥራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑን፣
- በሀገር ውስጥ ለሚማሩ መምህራን መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሊከፈላቸው የሚገባውን የትምህርት ድጋፍ ማለትም የትራንስፖርት አበል እና ለፅህፈት መሳሪያ እየከፈላቸው ቢሆንም፣ የሚከፈላቸው ጥቅማ ጥቅሞች ከሐምሌ 2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ድረስ በድምሩ ብር 280,492.21 የሥራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑን፣
- ትምህርት ሚኒስቴር የላካቸው የድህረ ምረቃ ትምህርታቸውን በመማር ላይ ያሉ ረዳት ምሩቃን ተማሪዎች የትራንስፖርት አበል እና ለፅህፈት መሳሪያ ግዥ የሚከፈላቸው ጥቅማ ጥቅሞች ከደመወዝ ጋር ተደምሮ ከሐምሌ 2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ድረስ የሥራ ግብር በድምሩ ብር 76,570.00 ያልተቀነሰ መሆኑን፣

በአጠቅላይ ብር 3,542,798.36 የሥራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

1.1.2 ስጋት፣

ማናቸውም ክፍያ ሲከናወን መቀነስ ያለበት ግብር ተቀንሶ አለመሰብሰቡ የመንግስት የበጀት አሸፋፈን ስርዓት ሊጎዳ ይችላል፡፡

1.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

መቀነስ ሲገባው ያልተቀነሰ የስራ ግብር ከሚመለከተቸው ሰራተኞች ተሰብስቦ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ ሊሆን ይገባል፡፡ ለወደፊትም እንደዚህ ዓይነት ስህተት እንዳይደገም የገቢ ግብር አዋጅ፣ መመሪያና ደንቦችን መሰረት ያደረገ አሰራር ሊከተል ይኖርበታል፡፡

1.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

- በፔይሮል ለመምህራን ከሚከፈሉት ጥቅማ ጠቅሞች የቤት አበል የኃላፊነት አበልና የትራንስፖርት አበል ሲሆን ከኃላፊነት ከቤት አበል የሥራ ግብሩ በአግባቡ የተቀነሰ ሲሆን ከተከፈላቸው ጥቅማ ጥቅም ከትራንስፖርት አበል ብቻ ታክስ ያልተቀነሰ ሲሆን ይህም መንግስት ለመምህራን የተመቻቸ የስራ ሁኔታ ለመፍጠር በተለየ ሁኔታ በመፍቀዱ የትራንስፖርት አበል እንደ ሌላ የኃላፊነት አበል ሳይሆን ከስራ ቦታ ወደ ቤትና ከቤት ስራ ቦታ ለመመላለስ ለታክስና ለሌሎች የትራንስፖርት ዓይነቶች ወጪ መሸፈኛ የተፈቀደላቸው ስለሆነ ከትራንስፖርት አበል ብቻ የስራ ግብር ሳይቀነስ ቢቀርም በመጀመሪያ ዙር የኦዲት ምርመራ ላይ ኦዲተሮች በሰጡት አስተያየት መሠረት ከሐምሌ 1/2009 ማለት ከ2010 በጀት ዓመት መጀመሪያ ጀምሮ ከትራንስፖርት አበልም ታክስ እየተቀነሰ መሆኑን እናረጋግጣለን፣ ለወደፊቱም ጥንቃቄ ይደረጋል፡፡
- በሀገር ውስጥ የሚማሩ የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ከተፈቀደላቸው የቤት አበል የትራንስፖርትና የጽ/መሣሪያ ክፍያ ከቤት አበል ብቻ የሥራ ግብር የተቀነሰ ሲሆን ግልጽ መመሪያ ስለአላገኘን ከትራንስፖርት፣ ከጽ/መሣሪያ እና አበል ክፍያ የሥራ ግብር ሳይቀነስ ሲከፈል ቢቆይም ከሐምሌ ወር 2009/2010 በጀት ዓመት ጀምሮ ከሚከፈላቸው ማንኛውም ጥቅማጥቅም ከወር ደመወዝ ጋር ተዳምሮ የተከፈላቸው መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡
- ከት/ሚኒስቴር የተላኩና የድህረ ምረቃ ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎች ከሚሰጣቸው የቤት፣ የጽሕፈትና የትራንስፖርት አበል ሲሆን ከጽሕፈት መሣሪያና ከትራንስፖርት አበል ታክስ ያልተቀነሱ ተማሪዎች ይህን አበል ለጽ/መሣሪያ ግዥ ለትራንስፖርት ስለሚጠቀሙ በሚል የሥራ ግብር አልተቀነሰም፡፡ በኦዲተር አስተያየት መሠረት ከሐምሌ 2009 ጀምሮ እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡

1.2.1 ግኝት፣ ከተለያዩ አቅራቢ ድርጅቶች መከፈል የነበረበት የጉዳት ካሳ፣

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ.ም አንቀጽ 16 በንዑስ አንቀጽ 16.27.3 በፊደል (ሸ) አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን አጠናቆ ባያስረክብ ለዘገየበት ጊዜ የሚወሰደው እርምጃ በንዑስ አንቀጽ 16.27.4 በፊደል (ሀ-ለ) አቅራቢው ሳይፈፅም በቀረው የውሉ መጠን ላይ በየቀኑ ወይም 1/1000 የጉዳት ካሳ እንደሚከፍል ሆኖ ከውሉ ዋጋ 10% የሚበልጥ መሆን እንደሌለበት ተገልጿል፡፡ የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የገዛቸውን የዕቃና የአገልግሎት ግዥዎች በውሉ መሰረት በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ገቢ ስለመሆናቸው እና አገልግሎት ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ አቅራቢዎቹ በውሉ መሰረት ዕቃውን አጠናቀው ሳያስረክቡ ላዘገዩበት የጉዳት ካሳ ብር 334,650.15 ተቀንሶ ገቢ አለመደረጉን ተረጋግጧል፡፡

1.2.2 ስጋት፣

ዩኒቨርሲቲው የገዛቸው ዕቃዎች በወቅቱ ቀርበው ገቢ ካልሆኑ ለታለመለት ዓላማ ላይውል ይችላል፡፡

1.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

አቅራቢዎች በወቅቱ ያላቀረቡበትን ምክንያት የሚገልጽ ማስረጃ ለኦዲቱ አልቀረበም፡፡ በመሆኑም አቅራቢዎቹ በውሉ መሰረት ዕቃውን አጠናቀው ሳያስረክቡ ለዘገዩበት የጉዳት ካሳ ሳይሰበሰብ የቀረው ተሰብስቦ ወደ መንግስት ካዝና ገቢ ሆኖ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊት ማንኛውም ግዥ መመሪያዎችን መሰረት ባደረገ መልኩ መከናወን አለበት፡፡

1.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

አቅራቢዎች በውል የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳያቀርቡ ሲቀሩ ለዘገዩበት ጉዳት ካሳ መከፈል ግዴታ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ አቅራቢዎች ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሲዘገዩ የዘገዩበት ምክንያት ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ አመልክቶ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍል ጋር በማጣራት የዘገዩበት ምክንያትና ተጨባጭና አሳማኝ ከሆነ ክፍያቸው ያለቅጣት እንዲከፈላቸው ከመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሲፈቀድላቸው ብቻ የተከፈለ ሲሆን በአብዛኛው ምክንያታቸው አሳማኝ ካልሆነ ባለው ደንብና መመሪያ መሠረት እየተቀጡ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

2. የወጪ ሂሳብ፣

2.1.1 ግኝት፣ ያለአግባብ የተከፈለ የትራንስፖርት አበል፣

መጋቢት 2007 ዓ.ም የወጣው የተሻሻለ የማቋቋሚያ አዋጅና ደንብ መሰረት የተመሰረተውን የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲን ለማጠናከር የፀደቀ መዋቅርና በጀት መሰረት ከተፈቀዱት ጥቅማ ጥቅሞች አንዱ የትራንስፖርት አበል እንደተገለጸው የትራንስፖርት አገልግሎት /አበል/ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች ከሥራው ባህሪ አንጻር በምርምርና ተዛማጅ ሥራዎች ምክንያት ከሥራ ሰዓት ውጭ የሚሰሩበት ሁኔታ ስለሚኖር ከቤት ወደ ሥራና እንደአስፈላጊነቱ ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስፈልገውን የትራንስፖርት ፍላጎት ለማሟላት የሚሰጥ አገልግሎት ወይም አበል ነው ይላል። አበሉ የተፈቀደው መምህራኑ እና የሥራ ኃላፊዎች በሥራ ላይ ሳሉ በትራንስፖርት ምክንያት እንዳይቸገሩና ሥራው እንዳይስተጓጎል ሲባል መንግስት የፈቀደው አበል ሲሆን፡ ዩኒቨርሲቲው በተፈቀደው መሰረት ስራ ላይ ማዋል ሲገባው፣

- በሀገር ውስጥ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የሚማሩ መምህራን የትራንስፖርት አበል፣ የቤት አበል እና ለጽህፈት መሳሪያዎች ግዥ የሚውል በተፈቀደው መሰረት በየወሩ እየተከፈላቸው ሲሆን፣ ከሥራ ውጭ ሆኖ ለትምህርት የተለያዩ ዩኒቨርሲቲ የገቡትን መምህራን በስራ ላይ ሆኖ ሲከፈላቸው የነበረው የትራንስፖርት አበል መቋረጥ ሲገባው፣ የትራንስፖርት አበል በተጨማሪ በድምሩ ብር 779,500.00 ከሐምሌ 2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ድረስ ያለአግባብ የተከፈለ መሆኑን ተረጋግጧል።
- በውጭ ሀገር በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የሚማሩ መምህራን በስራ ላይ ሆኖ ሲከፈላቸው የነበረው የትራንስፖርት አበል መቋረጥ ሲገባው፣ በድምሩ ብር **1,068,500.00** ከሐምሌ 2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ድረስ የትራንስፖርት አበል ያለአግባብ የተከፈለ መሆኑን ተረጋግጧል።

በአጠቃላይ ብር 1,848,000.00 በተፈቀደው መሰረት መከፈል ሲገባው ስራ ላይ ለሌሉት መምህራን ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል።

2.1.2 ስጋት፣

አለአግባብ የሚከናወን ማንኛውም ክፍያ ተጠያቅነትን ከማስከተሉም በተጨማሪ የመንግስትን ውስን ሀብት ለብክነትና ሊጋለጥ ይችላል።

2.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ከደንብና መመሪያ ውጭ የሚከናወኑ ማንኛውም ክፍያ ተቀባይነት እንደለሌው ታውቆ አለአግባብ የተከፈለው የትራንስፖርት አበል ተመላሽ ሆኖ ወደ መንግስት ካዚና ገቢ ሊሆን ይገባል። ለወደፊትም እንደዚህ አይነት ስህተት እንዳይደገም ማንኛውም ክፍያ ሲፈፀም ደንብና መመሪያን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ቁጥጥርና ክትትል ሊያደረግ ይገባል።

2.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በሃገር ውስጥ እና ውጭ ሃገር በተለያየ ዩኒቨርሲቲ የሚማሩ መምህራን የወር ደመወዛቸው ወርሃዊ ጥቅማጥቅም በሣይንስና ቴክኖሎጂ በኩል በተፈቀደላቸው መሠረት በየወሩ ከወር ደመወዛቸው ጋር ተደምሮ የሚከፈል የቤትና የትራንስፖርት አበል ሆኖ ለትምህርት ከሃገር ውስጥ ወደተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ሄደው ለሚማሩበት የኪስ ገንዘብ፣ የቤት አበል፣ የጽህፈት መሣሪያ እና ለትራንስፖርት እንዲከፈላቸው ከትምሃርት ሜኒስቴር በመጣው መመሪያ ሲሆን አንዱን ለይቶ አለመክፈል መመሪያ ስለሌለ ሲከፈል መቆየቱና በኦዲት ስራ ወቅትም በመውጫ ስብሰባ ላይ በግልጽ ለማስረዳት የተሞከረ ስለሆነ ለወደፊቱ ግልጽ መመሪያ ተጠይቆበት የሚስተካከል ይሆናል።

ውጭ ሃገር የሚማሩ መምህራን ባላቸው ውል መሠረት የወር ደመወዛቸው ግማሽ ማድረግ እንጂ የትራንስፖርት አበል ሌሎች ክፍያዎችን የሚከለክል ግልጽ መመሪያ ባለመኖሩ ክፍያ ሲፈጸመ የቆየ ቢሆንም ለወደፊቱ ከሚመለከተው አካል መመሪያ በመጠየቅ የሚስተካከል ይሆናል።

2.2.1 ግኝት፣ በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የተከፈለ የቤት አበል፣

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችና የደመወዝ ክፍያን በተመለከተ በ13/8/2003 ዓ.ም በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 የተጻፈ ደብዳቤ ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት የደመወዝ ስኬል እና ጥቅማ ጥቅም የሚወሰነው በሚኒስትሮች ም/ቤት እንደሆነ ገልጿል፡፡ በተጨማሪም ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እውቅናና ፈቃድ ውጭ ማንኛው በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ /በቦርድ/ የሠራተኞች የደመወዝ ስኬልና ጥቅማ ጥቅም መወሰን እንደማይችሉና ተግባራዊ እያደረጉ ያሉ መ/ቤቶች በአስቸኳይ እንዲያቋርጡ አሳስበዋል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በራሱ የአስተዳደር ካውንስል /Administrative council/ በ06/03/2008 በተያዘው ቃለ-ጉባኤ ለውጭ ሀገር ዜጋ መምህራን የቤት አበል 175 USD ሲከፈል የነበረውን 125 USD በመጨመር በወር

300 USD እንዲከፈላቸው ወስኖ እየተከፈለ መሆኑንና በአጠቃላይ ብር 2,112,407.70 በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝር ሁኔታው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተቁ	ቀን	የወጪ ደረሰኝ ቁጥር	ሂሳብ መደብ	የተከፈለ ብር (ETB)	የወቅቱ ምንዛሪ	በልዩነት የተከፈለው ገንዘብ		
						የተከፈለው የሰውብዛት እና ብር በዶላር	USD	ETB
1	29/11/08	JV-999151	6124	367,555.44	21.8783	125*56	7,000.00	153,148.10
2	28/12/08	JV-999153	6124	367,555.44	21.8783	125*55	6,875.00	150,413.31
3	30/01/09	JV999155	6124	354,866.03	21.8783	125*54	6,750.00	147,678.53
4	30/02/09	JV-999023	6124	363,165.00	22.01	125*55	6,875.00	151,318.75
5	30/03/09	JV999164	6124	417,749.80	22.01	125*64	8,000.00	176,080.00
6	30/04/09	JV999167	6124	441,300.50	22.01	125*67	8,375.00	184,333.75
7	27/05/09	JV-999172	6124	466,333.74	22.528	125*69	8,625.00	194,304.00
8	29/06/09	JV-999176	6124	425,557.70	22.5282	125*63	7,875.00	177,409.58
9	29/07/09	JV-999178	6124	418,799.24	22.5282	125*62	7,750.00	174,593.55
10	26/8/09	JV-999183	6124	427,909.50	22.6527	125*63	7,875.00	178,390.01
11	28/9/09	JV-999189	6124	507,647.01	22.6527	125*75	9,375.00	212,369.06
12	24/10/09	JV-999064	6124	509,685.75	22.6527	125*75	9,375.00	212,369.06
	ድምር							**2,112,407.70**

2.2.2 ስጋት፣

ማንኛውም ከደንብና መመሪያ ውጭ የሚከናወኑ ክፍያዎች የህግ ጥሰትን ከማስከተሉ በተጨማሪ የመንግስትን ውስን ሀብት ለብክነት ሊጋልጥ ይችላል፡፡

2.2.4 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው ማናቸውም ክፍያ ሲያከናውን ደንብና መመሪያን መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገበል፡፡ ስለዚህ ከደንብና መመሪያ ውጭ የሚመለከተው አካል ሳይፈቅድ የተከፈለው አግባብነት እንደሌለው ታውቆ ተመላሽ ሊሆን ይገባል፡፡ ለወደፊትም እንደዚህ አይነት ስህተት እንዳይፈጠር ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

2.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የቤት አበል ለውጭ ሃገር መምህራን ከተፈቀደው ውጭ ተከፍሎ መገኘት ለተባለው በዩኒቨርስቲያችን በተለያዩ ት/ቤቶች ተቀጥረው የሚሰሩ የውጭ ሃገር መምህራን ይከፈል የነበረው የቤት አበል ክፍያ ከኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር በተላከልን የክፍያ ሬንጅ 175-275 USD ሲሆን የአከፋፈሉ ሁኔታ ግን በምን

መልኩ መሆን እንዳለበት አይገልፅም። በመሆኑም የተለያየ የቤት አበል አከፋፈል ሲፈጸም የቆየ ሲሆን ይህ ደግሞ አነስተኛ የቤት አበል የሚከፈላቸው የውጭ ሀገር መምህራን ባቀረቡት ቅሬታ በግዜው በነበሩት የዩኒቨርስቲው ፕሬዝዳንት ተመሳሳይ እና ወጥ የሆነ ክፍያ ለመፈጸም ሲባል በአድሚኒስትሬቲቭ ካውንስል በተደረገው ስብሰባ ለሁሉም የውጭ ሃገር መምህራን 300 USD እንዲከፈላቸው በቀን 16 November 2015 G.C. ተወስኗል። በዚሁ መሰረት ለውጭ ሃገር መምህራን የቤት አበለ ከውሳኔው ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ 300 USD እየተከፈለ ይገኛል። በዚህ ጉዳይ ላይ በኦዲት መውጫ ስብሰባ ላይ በዝርዝር ለማስረዳት ተመክሯል።

2.2.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

በትምህርት ሚ/ር በተላከው የክፍያ መጠን ከ175 እስከ 275 የአሜሪካ ዶላር ባለው እንዲፈጸም መታዘዙ እየታወቀ፣ ተጠቃሚው ባመለከተው ቅሬታ በመነሳት በዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ውሳኔ መሠረት ክፍያ መፈጸሙ አግባብነት የለውም። በመሆኑም የሚመለከተውን አካል በማስፈቀድ ክፍያ መፈጸም ስለሚኖርበት በማሻሻያው መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል።

2.3.1 <u>ግኝት፣</u> <u>አለአግባብ የተከፈለ የቤት፣ የትራንስፖርት አበልና ደመወዝ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ዘርፍ ሰራተኞችን በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የድህረ ምረቃ ትምህርት እያስተማረ ይገኛል። በዚሁ መሰረት የሚከፈላቸው ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም እንዲሁም በገቡት ውል መሰረት ትምህርታቸውን አጠናቀው መመለስ ባለባቸው ጊዜ ውስጥ መመለስና አለመመለሳቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ትምህርታቸውን ያቋረጡ ወይም ያራዘሙ መምህራን ከሚማሩበት ተቋም ያቋረጡበትን ወይም ያራዘሙበትን ምክንያት የሚገልፅ የፅሁፍ ማስረጃ ሳያቀርቡ ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ሥራ ገበታቸው የሚመለሱበት ጊዜ ያለፈባቸው መምህራን ትምህርት ላይ እንዳሉ ተደርጎ የቤት አበል፣ የትራንስፖርት አበልና ደመወዝ በድምሩ ብር 802,291.00 ትምህርት ላይ መኖራቸው እና አለመኖራቸው ሳይረጋገጥ አለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል። ዝርዝር ሁኔታው እንደሚከተለው ቀርበዋል፦

ተቁ	ስም	ትምህርታቸውን የምጨርሱበት ጊዜ	የተከፈላቸው ደመወዝ እና ጥቅማጥቅም በወር	ጨርሰው መመለስ ከነበረባቸው ያለፉት ጊዜ በወር	ጠቅላላ የተከፈለ ብር
1	አብድልፈታህ አብደላ	8/01/09	9,735	8 (ከጥቅምት-ግንቦት)	9,735*8=77,880.00
2	አንዋር ደምሴ	8/2/09	9,735	7 (ከህዳር-ግንቦት)	9,735*7=68,159.00
3	ፍሬው ታደለ	12/2/09	11,310	7 (ከህዳር-ግንቦት)	11,310*7=79,170.00
4	ገብረ ሀይሌ ገ/እግዚአብሄር	12/2/09	11,310	7 (ከህዳር-ግንቦት)	11,310*7=79,170.00
5	ቴዎድሮስ እንዳለ	1/2/09	11,310	7 (ከህዳር-ግንቦት)	11,310*7=79,170.00
6	ይርዳው ጋሻው	23/10/08	9,054	1 ሐምሌ	9,045.00
			9,735	5 (ከነሐሴ-ታህሳስ)	9,735*5=48,675.00
7	መሰረት ታደሰ	19/03/09	11,310	7 (ከታህሳስ-ሰኔ)	11,310*7=79,170.00
8	በሬቻ ዳንደሳ	20/2/09	9110	7 (ከህዳር-ግንቦት)	9,110*7=63,770.00
9	ጌትነት ኡማ	4/1/09	11,310	8 (ከጥቅምት-ግንቦት)	11,310*8=90,480.00
10	ተስፋዬ ከበደ	20/12/08	9,735	9 (ከመስከረም-ግንቦት)	9,735*9= 87,615.00
11	ፍቃዱ ታረቀኝ	17/12/08	4443	9 (ከመስከረም-ግንቦት)	4,443*9=39,987.00
ጠቅላላ ድምር					802,291.00

2.3.2 ስጋት፣

ለትምህርት የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የሄዱ መምህራን ትምህርታቸውን ጨርሰው የሚመለሱበት ጊዜ ያለፈባቸው እና ትምህርት ላይ መኖራቸው እና አለመኖራቸው ሳይረጋገጥ ክፍያ መፈጸም ተጠያቅነትን ከማስከተሉም በተጨማሪ የመንግስትን ውስን ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

2.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ለትምህርት የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የሄዱ መምህራን ትምህርታቸውን ጨርሰው የሚመለሱበት ጊዜ ያለፈባቸው እና ትምህርት ላይ መኖራቸው እና አለመኖራቸው ሳይረጋገጥ የተከፈለ ክፍያ አግባብነት እንደለሌው ታውቆ ተመላሽ ሊሆን ይገባል፡፡ ለወደፊትም ስህተቱ እንዳይደገም ተጣርቶ ክፍያ መፈጸም አለበት፡፡

2.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ያለ አግባብ የተከፈለ ደመወዝና ጥቅማጥቅም በተመለከተ በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ለትምህርት ከላካቸው መምህራን መካከል ትምህርት የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የሄዱ መምህራን በተመለከተ፣ ትምህርታቸውን ጨርሰው ሳይመለሱ የቀሩ ለህግ ክፍል ተልከው ውሳኔ እየተጠባበቅን እንገኛለን የትምህርት እድል አግኝተው በገቡት የውል ጊዜ

ውስጥ ትምህርታቸውን ሳይጨርሱ የቀሩ ሌላው አሳማኝ ምክንያት አቅርበው በማኔጅመንት ውሳኔ ተጨማሪ የትምህርት ጊዜ የተሰጠባቸው መምህራንም አሉ አሁንም በውል ጊዜ ትምህርታቸውን ሳይጨርሱ የቆዩ ከሚማሩበት ት/ት ተቋም ተጨባጭ ማስረጃ ካላመጡ የሚከፈላቸው ደመወዝና ጥቅማ ጠቅም ክፍያ እየቀመ መሆኑንና የተከፈላቸውም ካሉ በህግ ክትትል እየተደረገና አንዳንዶቹ ዋሶቻቸው እንዲከፍሉ እየተደረገ ይገኛል፡፡

2.4.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ያለአግባብ የተከፈለ ደመውዝ፣</u>

ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ሚያዝያ 20/1990 ዓ.ም በቁጥር ጠ80.አጠ52/01/09 በተላለፈው መመሪያ መሰረት ውጭ አገር ለሚሄዱ የመንግስት ሠራተኞች በሙሉ በትምህርት ወይም በሥልጠና ለሚቆዩበት ሙሉ ጊዜ ግማሽ ደመወዛቸው እንደሚከፈላቸው ተወስኗል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በመመሪያው መሰረት ክፍያ ማከናወን ሲገባው፣ በደቡብ አፍርካ የሚማሩ መምህር ተስፋዬ ብርሃኔ ማሾ በመመሪያው መሰረት በየወሩ ግማሽ ደመወዝ መከፈል ሲገባው ሙሉ ደመውዝ በመክፈል ከሐምሌ 2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 2009 ዓ.ም በልዩነት ብር 62,139.00 ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

2.4.2 <u>ስጋት፣</u>

አለአግባብ የሚከናወን ማንኛውም ክፍያ የመንግስትን ውስን ሀብት ለብክነትና ሊያጋሊጥ ይችላል፡፡

2.4.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ያለአግባብ የተከፈለዉ ደመወዝ ተመላሽ ሆኖ ወደ መንግስት ካዚና ገቢ ሊሆን ይገባል፡፡ ለወደፊቱም እንደዚህ አይነት ስህተት እንዳይደገም ማንኛውም ክፍያ ሲፈፀም ደንብና መመሪያን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ቁጥጥርና ክትትል ሊያደረግ ይገባል፡፡

2.4.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ደቡብ አፍሪካ የፒኤችዲ ትምህርት ስለሚከታተሉ መምህር ተስፋዬ ብርሃኔ ጉዳይ ከአካዳሚክ ጉዳዮች ዲን ጋር በመነጋገር ከግል ማኅደራቸው አጣርተን ያለአግባብ ተከፍሎ ከሆነ ተመላሽ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡

2.5.1 <u>ግኝት፣</u> <u>በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የተከፈሉ ጥቅማ ጥቅሞች፣</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችና የደመወዝ ክፍያን በተመለከተ በ13/8/2003 ዓ.ም በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 የተጻፈ ደብዳቤ እንደሚገልጸው ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት የደመወዝ ስኬል እና ጥቅማ

ጥቅም የሚወሰነው በሚኒስትሮች ም/ቤት እንደሆነ ገልጿል፡፡ በተጨማሪም ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እውቅናና ፈቃፈድ ውጭ ማንኛው በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ /በቦርድ/ የሠራተኞች የደመወዝ ስኬልና ጥቅማ ጥቅም መወሰን እንደማይችሉና ተግባራዊ እያተደረጉ ያሉ በአስቸኳይ እንዲቋረጡ አሳስበዋል፡፡ ይሁን እንጂ የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ ከመመሪያ ውጭ የተለያዩ ክፍያዎችን እንደሚከተለው ከፍሎ ተገኝቷል፡-

- በዋና ግቢ የዓለም አቀፍ ሲምፖዚየም የሚቀርብ ወረቀቶችን ለከለሱት /proposal reviewer/ በሚል ለ45 መምህራን ለእያንዳንዱ መምህር ሁለት ወረቀት ለሰራው ለአንድ ወረቀት ብር 2,000.00 ሂሳብ በድምሩ ብር 180,000፣ የምርምር ፕሮጀክት የገመገሙት /reviewers/፣ ፋስሊቴት ያደረጉት /facilitators/ እና ሊቀመንበር /chairpersons/ በሚል 90 ለሚሆኑ ሠራተኞች ለእያንዳንዳቸው ከብር 750 እስከ ብር 2000.00 በመክፈል በድምሩ ብር 127,700.00፣ ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች ቴስስ ዲፌንስ ላይ ለተሳተፉ የውጭ እና የውስጥ ፈታኝ /internal and external eximaner/ በተማሪ ብር 1,500.00 ሊቀመንበር /chairperson/ በተማሪ ብር 750.00 በሚል በመክፈል በድምሩ ብር 253,500.00፣ ጥናታዊ ጽሑፍ ላቀረቡት፣ ለኮሚቴ፣ ለአመቻቹ፣ ለሊቀመንበር፣ ጥናታዊ ፅሑፍ ለገመገሙት እና ለዋና ኮሚቴ በሚል ለእያንዳንዳቸው ከብር 600.00-5,000.00 በመክፈል በድምሩ ብር 304,100.00፣ ለሌላ ጥናታዊ ፅሑፍ ለገመገሙት በሚል ለእያንዳንዳቸዉ ከብር 3,00.00-9,700.00 በመክፈል በድምሩ ብር 95,400.00፣ የዩኒቨርሲቲውን ስትራቴጂክ ዕቅድ ላዘገጁ ኮሚቴ በሚል ለ14 ሰው ለእያንዳንዳቸው 10,000.00 በድምሩ ብር 140,000.00፣ የማህበረሰብ አገልግሎትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ለግማሽ ቀን ለገመገሙት ለ16 ሠራተኞች ለእያንዳንዳቸው ከብር 2000-8000 በድምሩ ብር 58,000.00 በመክፈል፣ በአጠቃላይ ብር **1,158,700.00** በዋና ግቢ የተከፈለ መሆኑን፣
- በኤሌትሪካል ኢንጂነሪንግ ት/ቤት ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች ለቴስስ ዲፌንስ ለተሳተፉት ለውጭና ለውስጥ ፈታኝ /internal and external examiner/ በተማሪ ብር 1,500.00፣ ሊቀመንበር /chair person/ በተማሪ ብር 750.00፣

የመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም አማካሪ /advisor regular program/ በተማሪ ብር 4,320.00 በድምሩ ብር **446,640.50** የተከፈለ መሆኑን፣

- በሲቪል ኢንጂነሪንግ እና አርክቴክቸር ት/ቤት ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች ለቴስስ ዲፌንስ ለተሳተፉት ለውጭና ለውስጥ ፈታኝ /internal and external examiner/ በተማሪ ብር 1,500.00፣ ሊቀመንበር /chair person/ በተማሪ ብር 750.00፣ የመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም አማካሪ /advisor regular program/ በተማሪ ብር 4,320.00 በሚል በድምሩ ብር **205,755.33** የተከፈለ መሆኑን፣
- በአፕላይድ ተፈጥሮ ሳይንስ ት/ቤት ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች ለቴሲስ ዲፌንስ ለተሳተፉት ለውጭና ለውስጥ ፈታኝ /internal and external examiner/ በተማሪ ብር 1,500.00፣ ሊቀመንበር /chair person/ በተማሪ ብር 750፣ የመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም አማካሪ /advisor regular program/ በተማሪ ብር 4,320.00 በሚል በድምሩ ብር **317,620.00** የተከፈለ መሆኑን፣
- በመካኒካል ኬሚካልና ማቴርያልስ ኢንጂነሪንግ ት/ቤት ባለድህረ ምረቃ ተማሪዎች ለቴሲስ ዲፌንስ ለተሳተፉት ለውጭና ለውስጥ ፈታኝ /internal and external examiner/ በተማሪ ብር 1,500.00፣ ሊቀመንበር /chair person/ በተማሪ ብር 750፣ የመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም አማካሪ /advisor regular program/ በተማሪ ብር 4,320.00 በሚል በድምሩ ብር **98,574.27** የተከፈለ መሆኑን፣
- በዋና ግቢ ለ2009 ዓ.ም የምረቃ ኮሚቴ ለ52 ሠራተኞች ለእያንዳንዳቸው ከብር 2000-10,000 በመክፈል በድምሩ ብር 258,000.00፣ ከመደበኛ ስራቸው ውጭ በዲዛይን፣ በጨረታ ግምገማ፣ በግንባታ ቁጥጥርና ተያያዥ የኮንስትራክሽን ስራዎች ስለተሳተፉ ለሁለት መምህራን በየወሩ ብር 3,000 በመክፈል በድምሩ ብር 12,000.00፣ ለ2008 በጀት ዓመት ለሽልማት የተመረጡ ምርምር ፕሮጀክቶች በሚል ለ7 ባለሙያዎች ለእያንዳንዳቸው ከብር 7,500-20,000.00 በመክፈል በድምሩ ብር 90,000.00፣ በኢንዱስትሪ ዙሪያ ያሉትን የቴክኖሎጂ ችግሮችና ልዩነቶች መለየት ላይ ለተሳተፉት ለ28 መምህራን ለ15 ቀናት የውሎ አበል የተከፈላቸው ቢሆንም በተጨማሪ ለእያንዳንዳቸው በቀን 500 ብር 500*15*28 በድምሩ ብር 210,000.00፣ የተማሪዎች መመዝገቢያና መፈተኛ ሶፍትዌር ለሰሩ ሰራተኞ የማበረታቻ

በሚል ለ3 ሰው በድምሩ ብር 10,000.00፣ በቢሾፍቱ ለሰራተኞች በተሰጠው ስልጠና በሱፐርቫይዘሪነት ለተሳተፉት በሚል ለ22 ሰው ለእያንዳንዳቸው ከብር 1,200.00-4,000.00 በመክፈል በድምሩ ብር 44,800.00፣ ለአሽከርካሪዎችና ጋራጅ ሰራተኞች ስለትራፊክ ደህንነት ለአንድ ቀን ስልጠና ለሰጡት ለሁለት የትራፊክ ሰራተኞች ለእያንዳንዳቸው ብር 3,000.00 በድምሩ 6,000.00፣ የ2009 ዓ.ም አዳዲስ ተማሪዎች ቅበላና ምዝገባ ለማከናወን በ13 የፈተና ጣብያ ለፈታኝ መምህራን የውሎ አበል የተከፈላቸው ሲሆን በተጨማሪ ለ93 መምህራን ለእያንዳንዳቸው ብር 3,600.00 በድምሩ ብር 334,800.00፣ ለ3 አስተበባሪዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 8000.00 በድምሩ ብር 24,000.00፣ በተጨማሪም ለ2 አስተበባሪዎች 1500 እና 2500 በመክፈል በድምሩ ብር 4,000.00፣ የተማሪዎች መታወቂያ (ID) ያዘጋጁ እና በተማሪ ምዝገባ ስራ ለተሳተፉ ሰራተኞች ለ13 የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 5,000 በድምሩ ብር 65,000.00፣ የጣት አሻራ ማሽን ላገጠሙት በሚል ለ6 ባለሙያዎች ለእያነንዳንዳቸው ብር 5,000 በድምሩ ብር 30,000.00 እና በንብረት ቆጠራ ላይ ለተሰማሩ ቆጣሪዎች እና ሱፐርቫይዘሮች ማበረታቻ በሚል ለ65 ሰው ለእያንዳንዳቸው ብር 2,000.00 በድምሩ ብር 130,000፣ በአጠቃላይ ብር **1,218,600** የተከፈለ መሆኑ፣

በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው ብር **3,445,890.10** ደንብና መመሪያን መሰረት ያለደረገ በራሱ የክፍያ ስርዓት አውጥቶ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ያለአግባብ ክፍያ የፈጸመ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

2.5.2 <u>ስጋት፣</u>

ማንኛውም ከደንብና መመሪያ ውጭ የሚከናወኑ ክፍያዎች የህግ ጥሰትን ከማስከተል በተጨማሪ የመንግስትን ውስን ሀብት ለብክነትና ለምዝበራ ሊያጋልጥ ይችላለል፡፡

2.5.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው ማናቸውም ክፍያ ሲያከናውን ደንብና መመሪያን መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገበል፡፡ ስለዘህ ከደንብና መመሪያ ውጭ የተከፈለ አግባብነት እንደሌለው ታውቆ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱ ስህተቱ እንዳይደገም ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግበት ይገባል፡፡ በደንቡ መሠረት የሚመለከተውን አካል በማስፈቀድ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.5.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

- በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ከሚገኙት የአይሲቲ ሠራተኞች ለዩኒቨርሲቲው የሶፍትዌር ለመሥራት ለሁለት ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎች የመግቢያ ፈተና ለመመዝገብና ለመፈተን የሚያስችል ሶፍትዌር ላዘጋጁት የአይሲቲ ባለሙያዎች የተከፈለ ሲሆን ሥራው አድካሚና በሌላ ባለሙያ ቢሰራ ከፍተኛ ወጪ የሚያስወጣ በመሆኑ በውስጥ ባለሙያ መጠቀም ሆኖ ክፍያው ባለሙያዎቹ ጊዜአቸውን ወስደው ለሠሩበት የተከፈለ ሲሆን እንዲህ ዓይነት ክፍያዎች የሚከፈሉበት ሥርአት የሚዘረጋበት ሁኔታ እንዲመቻች ይደረጋል፡፡ በኦዲት አስተያየት መሠረት ለወደፊቱ ተገቢ ጥንቃቄ ይደረጋል፡፡
- የዩኒቨርሲቲያችን የተለያዩ የሥራ ክፍሎች የሥራ ላይ ክህሎታቸውን ለማሻሻልና በሙያቸው በየጊዜው ሥልጠና እንዲያገኙ ታቅዶ ለዚህም የሥልጠና በጀት ተይዞ ሲሰራ፣ የሥልጠና ሰነድ ዝግጅት፣ የሥልጠና ቦታና ጊዜ ማመቻቸት፣ አሰልጣኞች መጋበዝና ሥልጠና መስጠትና ለሚሰጥበት ጊዜ ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪ የሚንቀሳቀሱ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ከተያዘው የሥልጠና በጀት ክፍያ ስለሚያስፈልግ በሚያቀርቡት የሥልጠና ፕሮፖዛል መሠረት የተለያዩ ክፍያዎች ይፈጸማሉ፡፡
- በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የተለያዩ ጥናታዉ ጽሑፎች ይዘጋጃል፡፡ እነዚህ የተሰሩ ጥናቶች በተጨማሪ በባለሙያዎች ተገምግሞና ተተችቶ ከፀደቀ በኋላ ሥራ ላይ እንዲውል ስለሚደረግ ለዚህ ሥራ ደግሞ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ሲፈቀድ የተከፈለ ሲሆን በኦዲት አስተያየት መሠረት የአከፋፈሉ ሁኔታ /ተመን/ መመሪያ እንዲወጣለት ይደረጋል፡፡
- የዩኒቨርሲቲው የት/ት ተቋምና የምርምር ሥራ የሚሠራበት ሥራ ስለሆነ መምህራንና ባለሙያዎች ለሃገር ጠቃሚና ለማህበረሰቡ የሚጠቅሙ የተለያዩ ፕሮጀክቶችና ሥራዎች ለመሥራት ለተቀጠሩት መደበኛ ሥራ ተጨማሪ ሌሎች የሙያና የምርምር ሥራዎች ስለሚሠሩ ለዚህ ሥራ ደግሞ የሙያ ሥራ ክፍያ መከፈል ግዴታ ስለሆነ እንዲሁም መምህራኖች ባላቸው ሙያና እውቀት የዲዛይን ሥራ የጨረታ ዶክመንት ማጣራት ሌሎች ሥራዎችን ስለሚሠሩ በአሰሪና ኃላፊ ወይም በመ/ቤቱ የሥራ አመራር እየተወሰነ የሚከፈል ነው፡፡
- በዩኒቨርሲቲያችን አዲስ የሚገቡ ተማሪዎች ከየክልሉ የሚመረጡና በዚህ የፈተና ጣቢያዎች ተመርጠው ለፈተና የሚያስፈልጉ ዝግጅቶች ተደርገውና ምልመላውን ለሚያካሂዱ መምህራን ከአካባቢያቸው ውጭ በማስተባበር ሥራ ከመንግስት ሥራ ተጨማሪ ክፍያ እንደሚያስፈልግ ፕሮፖዛል ለዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት ቀርቦ አስፈላጊነቱ ከታመነበት በኋላ ክፍያ ተፈጽሟል፡፡

- ለማህበረሰብ አገልግሎት ቴክኖሎጂ ሽግግር የተለያየ ጥናትና ምርምር ሥራዎች የቀረቡትን ፕሮፖዛሎች በባለሙያ ተተችቶ የሚፀድቅ ሲሆን ለዚህ ሥራ /ግምገማ/ ሥራው አድካሚና የሙያ ሥራ ሲሆን እነዚህ የመርምር ሥራዎች በመማር ማስተማሩ ሥራ ላይ ተጨማሪ ሥራ ስለሆነ ክፍያዎች ፈጽሞ መሥራት ግዴታ ሆኖአል፡፡
- ከአስር ሺህ በላይ ተማሪዎች ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ በካርድ ለማዘጋጀት በባለሙያዎች የሚሠራና ከመምህራን ሥራ ሰዓት ውጪ በእረፍት ጊዜያቸው ጭምር የሚሠሩ በመሆኑ በውጪ ባለሙያ ቢሠራ ከፍተኛ ወጪ ሊያስወጣ የሚችል መሆኑን ግምት ውስጥ በመሆኑ የተከፈለ ነው፡፡
- ክፍያው የተፈጸመው የጣት አሻራ ለመግጠም ብቻ ሳይሆን በአይሲቲ ባለሙያ የተሰራው ለእያንዳንዳቸው ሠራተኛ ሕይወት ታሪክ /ፕሮፋይል/ ከሲስተሙ ጋር ለማስተዋወቅ ለተሠራ ሥራ የተከፈለ እንጂ የተገዛውን የጣት አሻራ ለመግጠም አልነበረም፡፡
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ብዛት ያለው ንብረት ቆጠራ ሲደረግ በዩኒቨርሲቲው ኃላፊዎች በተቋቋመ ኮሚቴና ጉዳዩ የሚመለከተው የሥራ ክፍል ሠራተኛ ሲሆን ይህ በመደበኛ ሥራ ሰዓት ብቻ ሊሠራ የማይችል ከስራ ሰዓት በዓልና ቀናትን ጨምሮ የሚሠራ በመሆኑ ክፍያ በማኔጅመንት ተወስኖ ተከፍሎአል፡፡ ለወደፊቱ ግልጽ መመሪያ እንዲኖር ከጥናትና መርምር እና ለመምህራን የሚከፈል የተለያየ ክፍያዎችን አስመልክቶ እንዲፈቀድልንና መመሪያ እንዲዘጋጅልን በሁለቱ ዩኒቨርሲቲ የተዘጋጀ ፕሮፖዛልና ጥያቄ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር አቅርበን በሂዳት ላይ ይገኛል፡፡

2.6.1 <u>ግኝት፣ በመንግስት በጀት ለሚተዳደሩ ተቋማት ያለአግባብ የተከፈለ ድጋፍ፣</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ግንቦት 1999 የወጣው የሂሳብ አወቃቀር መንግስት የፋይናንስ አካላትን እና ድርጊቶችን ለመለያት እና ለመመደብ የሚጠቀምበት የመለያ ቁጥር ስርዓት እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት በሂሳብ መደብ 6412 መዝግቦ ወጪ ማድረግ የሚቻለው ነፃ የአስተዳደር አቋም ላላቸው ተቋሞች በጥሬ ገንዘብ የሚከፈለውን ክፍያ እንዲሁም መንግስታዊ ላልሆኑ፣ የማህበራዊ፣ የሀይማኖት እና የበህል ተቋሞች የሚሰጠውንና ዝርዝር የሂሳብ መግለጫ የማይቀርብበት የገንዘብ እርዳታ እንደሆነና መንግስት ለበጎ አድራጎት እና ለሀይማኖት ድርጅቶቸ የሚሰጥ እርዳታ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በመንግስት በጀት ለሚተዳደሩ ተቋማት ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር ድጋፍ ብር 544,153.92 እና የአዳማ ከተማ አስተዳደር ለሚያዘጋጀው የ100ኛ ዓመት የምስረታ ክብረ በዓል ድጋፍ ብር 500,000.00 የተከፈለ ሲሆን፣ በድምሩ

ብር 1,044,153.92 ከደንብና መመሪያ ውጭ በመንግስት በጀት ለሚተዳደሩ ተቋማት ያለአግባብ ድጋፍ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

2.6.2 ስጋት፣

ከደንብና መመሪያ ውጭ የሚፈፅም ማንኛውም ክፍያ የመንግስት ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

2.6.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው ማናቸውም ክፍያ ሲያከናውን ደንብና መመሪያን መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገበል፡፡ ስለዘህ ከደንብና መመሪያ ውጭ የሚከፈል ክፍያ አግባብነት እንደለሌው ታውቆ ለወደፊት ስህተቱ እንዳይደገም ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

2.6.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

- የሣይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር በውጪ ሃገር ለሚታተም አጀንዳ የስፖንሰር ሽፕ ጥያቄ አቅርቦ በማኔጅመንት ተወስኖ ገንዘቡ ለሣይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡
- የአዳማ ከተማ አስተዳደር ከዩኒቨርሲቲው ጋር በተለያዩ ሥራዎች በማህበረሰብ አገልግሎት ከመሠረተ ልማት አቅርቦት በመሳሰሉት ከዩኒቨርሲቲው ጋር የሚሠራ ሲሆን ለከተማው 100ኛ ዓመት በዓል ዝግጅት ድጋፍ እንዲደረግ በማኔጅመንት በተወሰነው መሠረት ድጋፍ የተደረገ ነው፡፡ የድጋፍ አሰጣጥን አስመልክቶ ከገ/ኢ/ትብብር ሚ/ር በደረሰን መመሪያ መሰረት በ2010 በጀት ዓመት ሙሉ በሙሉ ተስተካክሏል፡፡

2.7.1 ግኝት፣ የመያዣ ሂሳብ ቋት እና ተቀጽላ ቋት ተከፍቶለት ያልተመዘገበ ስለመሆኑ፣

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ክፍል 7 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 28.5 በፍደል ለ/ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 16.26.9 ከተመለከተው በተጨማሪ ለማናቸውም የግንባታ ዘርፍ ስራ በክፍያ የምስክር ወረቀት መሰረት ከሚፈጸመው ከእያንዳንዱ ክፍያ ለግንባታ ሥራው ጥራት ዋስትና እንዲሆን 5% (አምስት በመቶ) በመያዣ መልክ ተቀንሶ ይያዛል ይላል፡፡ እንዲሁም በፊደል ሐ/ የግንባታ ሥራው ሲጠናቀቅ እና ጊዜያዊ ርክክብ ሲደረግ በዚህ አንቀፅ በፊደል ተራ (ለ) መሰረት ከተያዘው ገንዘብ ላይ 50% ለስራ ተቋራጩ ይለቀቃል ቀሪው 50% ለአንድ ዓመት የጥገና ጊዜ ተይዞ እንደሚቆይ በመመሪያው ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ የሥራ ተቋራጮች ጋር ውል ገብቶ ለሚያሠራው የግንባታ ሥራዎች ክፍያ ሲፈጽም በመመሪያው መሰረት ከሚፈጸመው ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ በውሉ መሰረት በየክፍያ ሰርተፊኬቱ የመያዣ ሂሳብ ተቀንሶ ቋት እና ተቀፅላ ቋት ተከፍቶለት የግንባታ

ሥራው ተጠናቆ የመጨረሻ ርክክብ እስኪደረግ ድረስ በመያዣነት ተመዝግቦ መያዝ ሲገባው፣

- በአፍሮ ፅዮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር የሥራ ተቋራጭ በግቢ ውስጥ ለሚያስገነባው ሁለገብ አደራሽ (Multipurpose Hall) እስከ 13ኛው የክፍያ ሰርተፍኬት የተሰራው ብር 85,250,865.26 ሲሆን፣ በዚህ የክፍያ ሰርተፊከት ብር 4,262,543.26 ቢታይም በመያዣ ሂሳብ ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑን፣
- በተክለ ብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር የሥራ ተቋራጭ በግቢ ውስጥ ለሚያስገነባው የምርምር ማዕከል (Research park project) እስከ 7ኛው የክፍያ ሰርተፊኬት የተሰራው ብር 260,085,753.68 ሲሆን፣ በ7ኛው የክፍያ ሰርተፊኬት ብር 13,004,287.69 ቢታይም በመያዣ ሂሳብ ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑን፣
- በአፍሮ ፅዮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር የሥራ ተቋራጭ በግቢ ውስጥ ለሚያስገነባው ስፖርት አካዳሚ (sport Academy) እስከ 11ኛው የክፍያ ሰርተፊኬት የተሰራው ብር 198,540,248.75 ሲሆን፣ በ11ኛው የክፍያ ሰርተፊኬት ብር 9,927,012.44 ምዝገባው ቢታይም በመያዣ ሂሳብ ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑን፣
- በኤፍኢ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር በግቢ ውስጥ ለሚያስገነባው የአስተዳደር ህንጻ ማዕከል (centeral Administration Buildig) በ6ኛው የክፍያ ሰርተፊኬት የተሰራው ብር 55,972,065.83 ሲሆን፣ በ6ኛው የክፍያ ሰርተፊከት ብር 2,798,,603.29 ቢታይም በመያዣ ሂሳብ ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑን፣
- በናታኢ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግል ማህበር በግቢ ውስጥ ለሚያስገነባው የስቲም ሴንተር (STEM center) እስከ 4ኛው የክፍያ ሰርተፊኬት የተሰራው ብር 8,355,932.96 ሲሆን፣ በ4ኛው የክፍያ ሰርተፊኬት ብር 417,796.65 ቢታይም በመያዣ ሂሳብ ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑን፣
- በናታኢ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግል ማህበር በግቢ ውስጥ ለሚያሰራው የግቢ ውበት (Compound Beautification) እስከ 2ኛው የክፍያ ሰርተፊኬት የተሰራው ብር 1,225,470.78 ሲሆን፣ በ2ኛው የክፍያ

ሰርተፊኬት የ2.5% ብር 30,636.77 ቢታይም በመያዣ ሂሳብ ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑን፣

- ዩኒቨርሲቲው በዝቋላ ኮንስትራክሽን ድርጅት የህንፃ እድሳትና ጥገና በግቢ ውስጥ ለሚያሠራው እስከ 8ኛው የክፍያ ሰርተፊኬት የተሰራው ብር 41,357,947.48 እና ብር 3,270,513.80 ሲሆን፣ በ8ኛው የክፍያ ሰርተፊኬት የ2.5%*38,087433.648 ብር 952,185.84 እና 5%*3,270,513.80 =163,525.69 በድምሩ ብር **1,115,711.53** ቢታይም በመያዣ ሂሳብ ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑን፣

በአጠቃላይ ብር **31,556,591.59** በመመሪያው መሰረት የመያዣ ሂሳብ ቋት እና ተቀጽላ ቋት ተከፍቶለት በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግቦ መያዝ ሲገባው ያልተያዘ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

2.7.2 ስጋት፣

የመያዣ ሂሳብ ተቀንሶ በተከፋይ ካልተያዘ የመጨረሻ የህንጻ ርክክብ ከተደረገ ለስራ ተቋራጮቹ ለመክፈል ሊያስቸግር ይችላል፡፡በተጨማሪም የመያዣ ሂሰቡ ተመዝግቦ ካልተያዘ ህንጻው ላይ ጉዳት ከደረሰ የመያዣ ሂሳብ ለመውረስ ሊያስቸግር ይችላል፡

2.7.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ከሥራ ተቋራጮች ጋር ውል ተገብቶ ለሚሰሩ ግንባታዎች በውሉ መሰረት የመያዣ ሂሳቦች ከእያንዳንዱ የክፍያ ሰርተፊኬት ላይ ተቀንሶ በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ ቋት እና ተቀጽላ ቋት ተከፍቶለት መመዝገብ አለበት፡፡

2.7.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የመያዣ ክፍያ /ሪቴንሽን/ አስመልክቶ በሂሣብ ምዝገባ አያያዝ ህግ (Accounting Principle) መሠረት ሪቴንሽን በሂሣብ ምዝገባ መታየት እንዳለበት ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ቀደም ብሎ ከገ/ኢ/ት/ሚ/ር በኩል ሪቴንሽን መመዝገቡ ተከፋይ ሂሣብ ስለሚያበዛ የመያዥያው ሂሣብ በክፍያ ሰርተፊኬት ላይ ብቻ እንዲታይና በሂሣብ ምዝገባ /Transaction/ ላይ ሳይታይ ክፍያው ብቻ ተመዝግቦ ለተያዘው ሪቴንሽን በየዓመቱ በጀት ተይዞለት የሪቴንሽኑ ክፍያ /ማስለቀቂያ/ ሲቀርብ ሂሣቡ ቀጥታ በወጪ ኮድ ተመዝግቦ እንዲከፈላቸው የተደረገ ሲሆን በየጊዜው የሚቀርበው የግንባታ ክፍያ የምንፈጽመው ከክፍያ ሰርተፍኬት ላይ ከጠቅላላ ክፍያ ሪቴንሽን ከተቀነሰ በኋላ በመሆኑ በሂሣቡ ላይ ተደጋጋሚ ክፍያ ሊያስከትል አይችልም፡፡ በኦዲት አስተያየት መሠረት ለወደፊቱ ከገ/ኢ/ት/ሜ/ር ጋር በመነጋገር ወደ ተክክለኛ የሂሣብ ምዝገባ ማምጣት ይቻላል፡፡

2.8.1 ግኝት፣ የግንባታ ሥራ በተቋሙ የግንባታ ጽ/ቤት የማማከር አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን፣

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ክፍል 7 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 28.5 በፊደል ሀ/ ለግንባታ ዘርፍ ስራ ክፍያ የሚፈጸመው የስራውን ደረጃ ተከትሎ ከአማካሪ መሃንዲስ በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት /Payment Certificate/ መነሻነት ብቻ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በግቢ ውስጥ ለሚያስገነባቸው የተለያዩ የግንባታ ስራዎች ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊነት ሊወስድ የሚችል የአማካሪነት ፍቃድ ባለው አማካሪ ድርጅት ቀጥሮ ማሰራት ሲገባው፣ በዩኒቨርሲቲው የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በአማካሪነት እና የክፍያ ሰርተፊኬት እንደሚያዘጋጅ ተረጋግጧል፡፡

- ዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች /Dormitory/ እድሳትና ጥገና ለመሰራት ከዝቋላ ኮንስትራክሽን ኮምፓኒ ጋር ዋና ውል ብር 39,299,078.32 ከተቀናሽ በኃላ (after rebate 4%) ብር 37,727,115.1872፣ (supplementary contract) ተጨማሪ ሥራ ውል ቁጥር-1 ብር 9,428,904.02፣ (variation order) የሥራ ለውጥ ትእዛዝ ቁጥር-1 ብር 1,245,733.10 ድምር ብር 48,401,752.31 ከተጨማሪ እሴት ጋር ጠቅላላ ውል **55,662,015.16** የግንባታ ስራ የማማከር ፍቃድ ሳይኖር በተቋሙ የግንባታ ጽ/ቤት የማማከር ሥራ እና የክፍያ ሰርተፊኬት ፀድቆ እንደሚዘጋጅ ተረጋግጧል፡፡
- ዩኒቨርሲቲው የ"STEM" ሴንተር ጥገና እና ግንባታ ሥራ ለማሰራት ከናተኢ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግ/ ማህበር ጋር ዋና ውል ብር 7,962,455.79፣ (supplementary contract) ተጨማሪ ሥራ ውል ቁጥር-1 ብር 1,854,210.29 እና (variation order) የሥራ ለውጥ ትእዛዝ ቁጥር-1 ብር 2,500,519.15 በድምሩ የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ብር 14,164,763.01 እና የግብ ውበት ሥራ ለማሰራት ከተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ብር 1,469,136.5 ውል የገባ ሲሆን፣ በአጠቃላይ ብር **15,633,899.51** የግንባታ ስራ የማማከር ፍቃድ ሳይኖር በተቋሙ የግንባታ ጽ/ቤት የማመከር ስራ እና የክፍያ ሰርተፊኬት ፀድቆ እንደሚዘጋጅ ተረጋግጧል፡፡

በጠቅላላው ብር **71,295,914.67** በመመሪያው መሰረት በግንባታ አማካሪ መሃንዲስ የማማከር ስራው መሰጠት ሲገባው፣ በተቋሙ የግንባታ ጽ/ቤት የማማከር ስራ እና የክፍያ ሰርተፊኬት እንደሚዘጋጅ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

2.8.2 ስጋት፣

ማንኛው የግንባታ ስራ መንግስት ባስቀመጠው ደንብና መመሪያ መሰረት ያማይከናውን ከሆነ ተጠያቅነትን ከማስከተሉ በተጨማሪ በግንባታ ስራዎች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊነት ሊወስድ የሚችል አካል ላይኖር ይችላል፡፡

2.8.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው ማንኛውም የግንባታ ስራ መንግስት ባስቀመጠው ደንብና መመሪያ መሰረት የማይከናውን ከሆነ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ስለሚችል በግንባታው ስራ ኃላፊነት ሊወስድ የሚችል በህግ የአማካሪነት ፍቃድ ባለው መሃንዲስ ማሰራት አለበት፡፡

2.8.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በዚህ የኦዲት ማስታወሻ ስር ከተገለጸው ግኝት አንጻር የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የ2008 ዓ.ም. የፋይናንስና የክዋኔ ኦዲት በሚከናወንበት ወቅት ተመሳሳይ ጥያቄዎች /ግኝቶች ተጠይቀው በግንባታ ፕሮጀክቶች ጽ/ቤታችን በኩል መልስ ተሰጥቶበት በወቅቱ የኦዲት ክዋኔን ሲያካሂድ ከነበሩ ኦዲተሮችና ኃላፊዎች ጋር ካጣቀሱት የግዥ እና ሌሎች ተዛማጅ የህግ አግባቦች ላይ መተማመን ባለመቻላችን ይህንኑ ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ለፌደራል ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ጽፈን በግኝቱ ላይ ማብራርያ የጠየቅንበትንና ከዚሁ አንጻር ከኤጀንሲው ያገኘነውን ምላሽ ከላይ ለተጠቀሰው የኦዲት ግኝትም ምላሽ ስለሚሆን 6 ገፅ አባሪ አድርገን ለማስረጃነት አቅርበናል፡፡

2.8.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

በግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ለዩኒቨርስቲው በጻፈው ምላሽ በዩኒቨርስቲው መሐንዲሶች ሊሠራ የሚችል ከሆነ ሌላ አማካሪ የመቅጠር ግዴታ እንደሌለ፣ እንዲሁም የማማከር ሥራው በመሐንዲሶቹ መሠራቱ ያስከተለው ችግር ካለ ግን እንደ ኦዲት ግኝት ሊቆጠር እንደሚችል በደብዳቤው ገልጿል፡፡ ሆኖም በደንቡ የማማከር አገለግሎት ለመስጠት የማማከር ፍቃድ ፍቃዱን ከሚሰጠው አካል ሊያገኝ እንደሚገባ ተገልጿል፡፡ የማማከር ሰርተፊኬት የሌለው ግለሰብም ሆነ ድርጅት ለሚሰጠው የማማከር አገልግሎት ላይ ችግር ቢገጥም ተጠያቂ ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም ደንቡ በሚፈቅደው መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን ይገባዋል፡፡

2.9.1 ግኝት፣ የሌተር ኦፍ ክሬዲት /letter of Credit/ ሂሳብ ምዝገባን በተመለከተ፣

የፌዴራል መንግስት የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር መመሪያ ግንቦት 1999 ዓ.ም የወጣው የወጪ ሂሳብ መደቦች ወጪ የሚደረግባቸውን የሂሳብ መደቦች መግለጫ በዝርዝር

ተቀምጧል፡፡ በዚሁ መሰረት ዩኒቨርሲቲው በዓለም አቀፍ ስምምነት መሰረት በባንክ በኩል በሌተር ኦፍ ክሬዲት /letter of Credit/ ከፍተው ግዥ ለሚፈጽማቸው የላቦራቶሪ ዕቃዎች እና የህትመት ማሽን በትክክል ስለመመዝገቡ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ዩኒቨርሲቲው የላቦራቶሪ ዕቃዎች እና የህትመት ማሽን ለመግዛት ከ2006 ዓ.ም እስከ 2009 ዓ.ም የሌተር ኦፍ ክሬዲት /letter of Credit/ በዓለም አቀፍ ስምምነት በባንክ በኩል ለተከፈተው ሌተር ኦፍ ክሬዲት /letter of Credit/ ለገባው ዋስትና የሚተላለፈውን ገንዘብ ለዚህ ተብሎ ለተያዘው በሂሳብ መደብ 4104 መመዝገብ ሲገባው፣ ለዕቃ አቅራቢዎች የሚፈጸም የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የሚመዘገብበት በሂሳብ መደብ 4253 ብር **18,297,434.93** የተያዘ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

2.9.2 ስጋት፣

በሌተር ኦፍ ክሬዲት መያዝ ሲገባው ለዕቃ አቅራቢዎች የሚፈጸም ቅድሚያ ክፍያ የሚመዘገብ ከሆነ የአቅራቢዎችን ቅድሚያ ክፍያ መጠን ከፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2.9.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንገግስት የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር ስርዓት መሰረት ባደረገ አሰራር ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ለአቅራቢዎች ያልተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ እንደተሰጠ ተደርጎ የሚመዘገብ ከሆነ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳቦችን ሊያሳብጥና ሂሳቡንም ለመከታተል ስለሚችል በተያዘለት ሂሳብ መደብ መመዝገብ አለበት፡፡

2.9.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በአለም አቀፍ ጨረታ ስምምነት መሰረት LC ሲከፈት አቅራቢው ድርጅት ያሸነፈበት ዕቃ ዋጋ በባንክ በኩል ቢከፈልም ንብረቱ ሞዴል 19 ተቆርጦበት ገቢ እስካልሆነ ድረስ ባንክ ከሂሣባችን የቀነሰውን ሂሳብ ለመመዝገብ በተሰብሳቢ መያዝ ስለአለበት በተሰብሳቢ ሂሣብ መደብ 5253 ተመዝግቦ የቆየ ንብረቱ በሞዴል 19 ገቢ ሲሆን የወጪ ሂሣብ መደብ ይዞ የሚመዘገብ ስለሆነ መጀመሪያ LC ሲከፈት በ4253 እንዲያዝ ተደርጓል፡፡

2.10.1 ግኝት፣ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበ ድርጅት የተፈጸመ ግዥ፣

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ-28 ንዑስ አንቀጽ አንድ በማንኛውም የመንግስት ግዥ ለመሳተፍ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከፊደል ሀ-ሰ የተዘረዘሩትን እና የመንግስት መ/ቤቶች ከግዥው ልዩ ባህርይ በመነሳት የሚያወጧቸውን ሌሎች መስፈርቶች ማሟላት እንዳለበት ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ.ም

ተጫራቾችን ከጨረታ ውጭ ማድረግ የሚቻለው በአንቀጽ-16 ንዑስ አንቀጽ 16.21 ከፊደል ሀ-ረ ከተገለጹት ጥፋቶች ውስጥ አንዱን የፈጸመን ተጫራች የመንግስት መ/ቤቱ ከጨረታ ውጭ ማድረግ እንደሚችል ተቀምጧል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፡

- ለተማሪዎች የምግብ አገልግሎት የሚውል የከብትና የበግ ሥጋ ግዥ ለመፈጸም ባወጣው ግልጽ ጨረታ ዋጋ የሰጡት ሁለት ድርጅቶች ብቻ ሲሆኑ፣ ከሁለቱ ዝቅተኛ ዋጋ የአቀረበው ሞሊሶ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ ቢሆንም፣ ዩኒቨርሲቲው ካስቀመጣቸው የመገምገሚያ መስፈርቶች ውስጥ አንዱ ድርጅቶቹ ቢያንስ ሁለት ዓመትና ከዚያም በላይ የስራ ልምድ ማቅረብ አለባቸው የሚል ሲሆን፤ ሞሊሶ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ ለረጅም ዓመት ለተለያዩ ተቋማትና ዩኒቨርሲቲ የስጋ ግብዓት ሲያቀርብ እንደነበረ ማስረጀው ያሳያል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ታምራት ተሾመ በ2006 ዓ/ም ለአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ኢንተርፕራይዝና ለአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ለአንድ ዓመት እንዳቀረበ ማስረጃው ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ በተቀመጠው የግምገማ መስፈርት የስራ ልምድ 20% ያለው ሲሆን፣ ዩኒቨርሲቲው በቴክኒክ ግምገማው በስጋ አቅርቦት ረጅም ዓመት ስራ ልምድ ያለው ድርጅት ዜሮ ነጥብ በመስጠት የቴክኒክ ግምገማውን እንዲወድቅ ተደርጎ ዝቅተኛ ወይም አንድ ዓመት የስራ ልምድ ያለውና ከፍተኛ ዋጋ አቅራቢ የሆነውን ታምራት ተሾመ አሸናፊ ተደርጎዋል፡፡ ሞሊሶ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ ያቃረበው ጠቅላላ ዋጋ የተጨማሪ እሴትን ጨምሮ ብር 5,710,173.20 ሲሆን፣ ታምራት ተሾመ ያቀረበው ጠቅላላ ዋጋ ደግሞ ብር 6,634,104.94፣ ከሞሊሶ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ ግዥው ቢፈጸም ያለው ልዩነት ብር 6,634,104.94-5,710,173.20 ብር **923,931.74** መንግስት ማግኘት የሚገባውን ገንዘብ እንድያጣ ተደርጓል፡፡
- ለሲቪል ኢንጅነሪንግ ለመማር ማስተማር የሚያገለግሉ ግብአቶች እና ተያያዥ አገልግሎቶችን ግዥ በመፈጸም ብር 144,095.00 ክፍያ የፈጸመና ከዚህ ውስጥ ገመድ ሴቲንግ አውት ጥቅል ላይ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበዉ ፍሪክ አስመጪና ላኪ ሆኖ ሳለ ከፍተኛ ዋጋ ከአቀረበው ቢኒያም ተስፋዬ ግዥ የተፈፀመ ሲሆን ፤ዝቅተኛ ዋጋ ከተጨማሪ እሴት ጋር ብር 74.52 የዕቃ ብዛት 60 ሲሆን፤ ከፍተኛ ዋጋ ያቀረበው ደግሞ ብር 218.5 ብዛት 60 ልዩነት 218.5*60 =13,110 — 74.52*60 =4,471.20 ብር

8,638.80 ዩኒቨርሲቲዉ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት ግዥ በመፈጸሙ መንግስት ማግኘት የሚገባውን እንዲያጣ መደረጉን፣

በአጠቃላይ ብር 932,570.54 ዝቅተኛ ዋጋ አቅራቢ ድርጅት እያለ ከፍተኛ ዋጋ አቅራቢ ከሆነው በመገዛቱ መንግስት ማግኘት የሚገባውን ገንዘብ እንድያጣ ተደርጓል፡፡

2.10.2 ስጋት፣

ከመንግስት ውስን ሀብት የሚመጣ በጀት በአግባቡና ወጪ ቆጣቢ በሆነ አሰራር ተግባራዊ ካልተደረገ የመንግስት ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

2.10.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማናቸውም የዕቃ ግዥም ሆነ የአገልግሎት ግዥ ማከናወን ያለበት የመንግስትን ደንብና መመሪያ መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ ስለዚህ ለወደፊት መሰል ስህተት እንዳይፈጠር ትኩረት ተሰጥቶበት ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

2.10.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት ለተማሪዎች የምግብ ግብአት አገልግሎት የሚውል የከብትና የበግ ሥጋ ግዥ ለመፈጸም ባወጣው ግልጽ ጨረታ ላይ ሞሊሶ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማናታምራት ተሸመ የተወዳደሩ ሲሆን በተቀመጠው የመወዳደሪያ መስፈርት የቴክኒክ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሰነዱንና በአካል በቦተው ተገኝተው በቀረበው የጥናት ሪፖርት መሰረት መሊሶ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ ከተቀመጠው የማለፊያ ነጥብ በታች ውጤት በማምጣቱ ወደ ቀጣይ ሊያልፍ ያልቻለ በመሆኑና ድርጅቱም ቅሬታ አቅርቦ ተገቢ ምላሽ የተሰጠበት 2 ገጽ ማስረጃ የተያያዘ መሆኑን እየገለጽን በቴክኒክ ምዘና ያላለፈን ተወዳዳሪ ያቀረበውን ፋይናንሽያል ኦሪጅናል ሰነድ ከፍቶ በማየት አሸናፊ ነው ብሎ መደምደም አስቸጋሪ መሆኑን ነው፡፡

የገመድ ሴትንግ አውት ጥልቅ ግዥን በተመለከተ የተገኘ ኦዲት ግኝት ትክክለኛ በመሆኑ ለወደፊቱ ጥንቃቄ ለማድረግ ትምህርት የሰጠን ስለሆነ ለማረም እንደምንሠራ አረጋግጣለሁ፡፡

2.11.1 ግኝት፣ ከደንብ ውጭ በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ፣

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምዕራፍ-6 አንቀጽ-51 ንዑስ አንቀጽ /1/ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት በፊደል /ሀ/ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው፣ የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል

መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያን እንደገና ለማሻሻል ታህሳስ 2008 ዓ.ም የወጣ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 25.7 በፊደል /ሀ/ የመንግስት መ/ቤቶች በግዥ እቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ዋጋቸው ከብር 5,000.00 ያልበለጡ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን በቀጥታ ግዥ ከማናቸውም ሻጭ ድርጅት መፈጸም ይችላሉ፡፡ ሆኖም የግዥዎች ድምር በአንድ በጀት ዓመት ውስጥ ከብር 75,000.00 መብለጥ እንደሌለበት ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በአዋጁ መሰረት አገልግሎቱ ከአንድ አቅራቢ ብቻ የሚገኝ በመሆኑ ማወዳደር ያልቻለ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ሳያቀርብ እና የመንግስት ሀብት ቆጣቢ በሆነ መልክ ግዥውን ማከናወን ሲገባው፤

- በዋና ግቢ የተሸከርካሪ የጥገና አገልግሎት ግዥ ከሞኤንኮ፣ አግታ፣ ኒያላ ሞተርስ፣ ከኦርቢስ፣ ኤክሲድ አውቶሞቲቭ፣ ከፖል ሪዩስና ልጆቹ እና ከኢትዮሌክስ በድምሩ ብር 1,671,778.79፣ የመስተንግዶ አገልግሎት ኬቤኪ ባርና ሬስቶራን ብር 138,862.50፣ አዩ ኢንተርናሽናል ብር 125,314.79፣ ሪፍት ቫሊ ሆቴል ብር 42,087.97፣ አደማ ሪል እስት፣ ዳሎል ሆቴል ብር 62,110.23፣ አዳማ ጀኔራል ሆስፒታል ብር 285,154.00፣ ከአዳማ ኢንተርፕራይዝ ብር 156,768.29፣ ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብድርና ቁጠባ ህ/ሥ/ማ ብር 241,932 የመስተንግዶ ድምር ብር 1,052,229.78 በአጠቃላይ ብር **2,724,008.57** በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፣
- በሲቪል ኢንጂነሪንግ እና አርክቴክቸር ት/ቤት የሆቴል መስተንግዶ አገልግሎት ግዥ ብር 67,964.36 በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፤
- በኤሌትሪካል ኢንጅነሪንግ ት/ቤት የቀጥታ የሆቴል መስተንግዶ አገልግሎት ግዥ ብር 62,361.97 በቀጥታ ግዥ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡
- በአፕላይድ ተፈጥሮ ሳይንስ ት/ቤት የቀጥታ የሆቴል መስተንግዶ አገልግሎት ግዥ ብር 75,457.95 በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ ሲሆን፣

በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው ብር **2,929,792.85** በቀጥታ ግዥ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

2.11.2 ስጋት፣

ማንኛውም ግዥ በአዋጅ፤በመመሪያና ደንብ መሰረት የማይከናወን ከሆነ የህግ ጥሰት ከማስከተሉም በተጨማሪ የመንግስት ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

2.11.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ግዥዎች በቀጥታ ከተወሰነ አቅራቢዎች ብቻ የሚገዛ ከሆነ ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ሊከናወን ስለማይችል እና ግዥው ፍትሐዊ እንድሆን ሁሉንም አቅራቢዎች በሚያሳትፍ መልኩ የግዥ አዋጅናመመሪያዎችን መሰረት በማድረግ መከናወን አለበት፡፡

2.11.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

- ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብድርና ቁጠባ ህ/ሥ/ማ የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ ለመፈጸም የቻልነው ስልጠና ለመስጠት በድንገት ከፓርላማ እንግዶች እንደዛሬ የገቡ ስለሆነ ነገ ለሁሉም ተሳታፊዎች ውሃ በቀን ሁለት ጊዜ ማቅረብ ግዴታ ስለሆነ ውሃ አቅራቢ ነጋዴዎች አወዳድረን ግዥ ለመፈጸም ግማሽ ቀን ብቻ ስለነበረን ከዩኒቨርሲቲው ብድርና ቁጠባ ህ/ሥ/ማ ቀጥታ ግዥ እንዲደረግ ተደርጓል፡፡
- የተሽከርካሪ ጥገና አገልግሎት ቀጥታ ግዥዎች የተፈጸመው የዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት ከአስመጭ ኩባንያዎች የቀጥታ መለዋወጫ ዕቃዎችና ጥገና አገልግሎት እንዲፈጸም በወሰነው መሰረት ሲሆን ይህ አሰራር በየአመቱ የኦዲት ግኝት ሆኖ በመገኘቱ በ2010 የበጀት ዓመት የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ አስፈቅደን የቀጥታ አገልግሎት እያገኘን እንገኛለን (አራት ገፅ ማስረጃ ተያይዟል)
- ከኪቤክና የአዳማ ጀነራል ሆስፒታል የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ በተመለከተ በወቅቱ አስቸኳይ ሁኔታና በግልፅ ጨረታ ሂደት ለማከናወን ግዜ የማይሰጥ ሁኔታ በማጋጠሙ በዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት ውሰኔ መሰረት የተፈጸመ ቀጥታ ግዥ ነው፣
- ከአዩ ኢንተርናሽናል የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ በተመለከተ ለምሳ ግብዣ ተወዳድሮ ያሸነፈው ድሬ ኢንተርናሽናል በዕለቱ ምሳ ባለማዘጋጀቱ ድንገተኛ ያልታሰበ ስለሆነ ተሰብሳቢ እንግዶች ያለምሳ እንዳይውሉ ታስቦ የተፈጸመ ነው፣
- ዳሎል ሆቴል የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ በተመለከተ ለመማር ማስተማር አገልግሎት የሚውሉ የላብራቶሪ ዕቃዎች የቴክኒክ ምዘና ከአራቱም እስኩሎች የተውጣጡ ኮሚቴዎች የመስተንግዶ አገልግሎት ያገኙበት ሲሆን በአጭር ቀን ተሰርቶ ያልቃል ተብሎ ቢታሰብም ረጅም ጊዜ በመውሰድ የተፈጸመና ትክክለኛ የኦዲት ግኝቶች መሆናቸውንና ወደፊት የምናርመው ይሆናል፣
- ኢንተርፕራይዙን በወቅቱ ዩኒቨርሲቲው ያቋቋመና የመንግስትም አካል ስለሆነ የሚወጣው ገንዘብ ከአንድ የመንግስት ካዝና ወደ ሌላው የመንግስት በካዝና ተብሎ ስለሚታመን ለትርፍም ሳይሆን አገልግሎት ለመስጠት የተመሰረተ መሆኑ ግንዛቤ ተወስዶ የተፈጸም ግዥ ነው፡፡

2.12.1 ግኝት፣ በውስን ጨረታ የተፈጸመ ግዥ፣

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ሰኔ 2002 አንቀጽ 23 ውስን ጨረታ ግዥ አፈፃፀም ንዑስ አንቀጽ 23.2.1 ፊደል ሀ በተገለጸው መሰረት ዕቃው የግንባታ ዘርፍ ስራው ወይም አገልግሎቱ ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝ ሲሆን የጨረታ ጥሪው በደብዳቤ ለሁሉም አቅራቢዎች በአድራሻቸው ተዘጋጅቶ መላክ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በመቀጠልም በንዑስ አንቀጽ 23.4 ግዥን በውስን ጨረታ ለመፈጸም በፊደል ሀ/ ግዥውን ለመፈጸም የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ቢያንስ ለሁለት ጊዜ ወጥቶ ምንም ተጫራች ያልቀረበ ወይም በድጋሚ በወጣ የቀረቡት ተጫራቾች በመ/ቤቱ የተዘጋጀውን የቴክኒክ ፍላጎት ያላሟሉ መሆኑን ሲረጋገጥ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ብዙ አቅራቢዎች መኖሩን እያወቀ ወይም ውስን አቅራቢ ስለመሆናቸው ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ሳይቀርብ የመጋረጃ ግዥ ከዮሴፍ ከበደ ጨርቃ ጨርቅ መደብር በውስን ጨረታ ግዥ በመፈጸም ብር 527,745.14 ክፍያ የፈጸመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

2.12.2 ስጋት፣

ከመንግስት ደንብና መመሪያ ውጭ የሚከናወኑ ግዥዎች የህግ ጥሰትን ከማስከተል በተጨማሪ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

2.12.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማናቸውም የዕቃ ግዥም ሆነ የአገልግሎት ግዥ ማከናወን ያለበት የመንግስትን ደንብና መመሪያ መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ ከደንብ እና ከመመሪያ ውጭ የሚከናወን የዕቃም ሆነ የአገልገሎት ግዥ ተቀባይነት እንደሌለው ታውቆ ደንብና መመሪያን መሰረት ያደረገ አሰራር ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡

2.12.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የመጋረጃ ውስን ጨረታ በተመለከተ አዲሱ የአስተዳደር ህንጻ በመጠናቀቁ የተለያዩ የስራ ክፍሎች በአስቸኳይ ከአሮጌው አስተዳደር ህንጻ ወደ አዲሱ እንዲገቡ በሚደረጉት የገቡት ሰራተኞችም በፀሀይ ሀይል ምክንያት በመቃጠላቸውና ስራቸውን መስራት ስላልቻሉ የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራሮች (AC) በውስን ጨረታ ግዥ እንዲፈጸም በመወሰኑ ነው::

2.13.1 ግኝት፣ ግዥዎችን ቆራርጦ በዋጋ ማቅረቢያ የተፈጸመ ግዥ፣

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 24.1/ የአዋጁ አንቀጽ 55 እና 56 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የመንግስት መ/ቤቶች አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ ግዥን በግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈፀም አለባቸው፡፡ ሆኖም

ሊታቀዱ ያልቻሉና ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ እና ዋጋቸው በንዑስ አንቀጽ 24.2 በተመለከተው ገደብ ውስጥ ይሆናል ተብሎ የሚገመቱ ግዥዎችን በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ዘዴ ለመፈፀም ይችላሉ ይላል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው የግዥ ፍላጎትን አሰባስቦ ከመግዛት ይልቅ በርካታ ግዥዎችን ቆራርጦ በዋጋ ማቅረብያ ግዥ የፈጸመ ሲሆን፣

- በዋና ግቢ የፈርኒቸር ግዥ ብር 691,827.25፣ የወለል ምኝጣፍ ግዥ ብር 354,637.00፣ የመጋረጃ ግዥ ብር 799,913.32፣ የታብሌት ግዥ ብር 96,600.00፣ የፕሪንተር ሄድ ግዥ ብር 89,010.00፣ የጥገና ዕቃዎች ግዥ ብር 309,580.00 በድምሩ ብር **2,341,567.57** አንድ ላይ አሰባስቦ ግዥ መፈጸም ሲገባ ቆራርጦ በዋጋ ማቅረቢ ግዥ የተፈጸሙ መሆኑን፣
- በኤሌትሪካል ኢንጅነሪንግ ት/ቤት፣ የፈርኒቸር ግዥ ብር 10,909.99፣ የእስቴሽነሪ ዕቃዎች ግዥ ብር 367,333.00፣ የመጋረጃ ዕቃዎች ግዥ ብር 312,014.09፣ በድምሩ ብር 690,257.08 በዋጋ ማቅረቢ ግዥ የተፈጸመ መሆኑን፣
- በሲቪል ኢንጂነሪንግ እና አርክቴክቸር ት/ቤት፣ የፈርኒቸር ግዥ ብር 54,441.00፣ የፕሎተር ዕቃዎች ግዥ ብር 327,779.00፣ የመጋረጃና ምንጣፍ ዕቃዎች ግዥ ብር 104,037.05፣ በድምሩ ብር **486,257.05** በዋጋ ማቅረቢ ግዥ የተፈጸመ መሆኑን፣
- በአፕላይድ ተፈጥሮ ሳይንስ ት/ቤት የፈርኒቸር ግዥ ብር 67,261.66፣ የእስቴሽነሪ ዕቃዎች ግዥ ብር 87,205.88፣ የመጋረጃ ዕቃዎች ግዥ ብር 30,636.00፣ በድምሩ ብር **185,103.54** በዋጋ ማቅረቢ ግዥ የተፈጸመ ግዥ ሲሆን፣

በአጠቃላይ ብር **3,703,185.24** አንድ ላይ አሰባስቦ ግዥ መፈጸም ሲገባው፣ ተቆራርጠው በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ የተፈጸመ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

2.13.2 ስጋት፣

የግዥ ሰርዓትን በጠበቀ መልኩ ግዥ አለማከነወን መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግና ደንብና መመሪያ ሊጣስ ይችላል፡፡

2.13.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ግዥን ቆራርጦ መግዛት የመንግስት ገንዘብን ለብክነት እና ለከፍተኛ ወጪ ስለሚዳርግ የየክፍሉን የግዥ ፍላጎት በማሰባሰብ ግዥ ቢፈጽም በርካታ ተሳተፊ ድርጅቶች በወድድር

ስለሚቀርቡና ከዋጋም አኳያ ዝቅተኛ ዋጋ ሊቀርብ ስለሚችል የመንግስት ወጪ ሊቀንስ ይችላል፡፡

2.13.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በዋጋ ማቅረብያ ግዥ የተፈፀሙ መጋረጃዎችና ምንጣፎች በአመቱ ዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱና ያልታሰቡ የአስቸኳይ ግዥ ጥያቄዎች በመሆናቸው፣ 1, በዩኒቨርስቲው በ 2009 የበጀት አመት በኢትዮጵያውንና የውጭ አገር ዜጎች የሚማሩ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ልዕቀት ማዕከላት በመቋቋማቸውና የሚሰሩበትም ቢሮዎች በአዲስ መልክ የተደራጁ በመሆኑ የመጋረጃ የምንጣፍና የፈርኒቸር ግዥዎች ሟሟላት ያለባቸው ይሟላ በሚል ጫና ስለነበረ በዋጋ ማቅረብያ ግዥ ለመፈፀም የተገደድንበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ 2, አዲሱ የአስተዳደር ህንፃ ተገንብቶ በመጠናቀቁና አሮጌ አስተዳደር ህንፃ እንዲገቡ በመደረጉ የመጋረጃ የምንጣፍና የፈርኒቸር ግዥዎች በአመቱ ዕቅድ ውስጥ በመካተታቸው ያልታሰበ ድንገተኛ ጥያቄ በመሆኑ በግልፅ ጨረታ ግዥ እንዲፈፀም የተለያዩ የስራ ክፍሎች በባዶ ቢሮ የገቡበት ሁኔታ በመፈጠሩና ጨኸት ስለነበር በዋጋ ማቅረብያ ግዥ በመፈፀም ችግሩን ለመፍታት ጥረት ተደርጓል መንግስት ላላስፈላጊ ወጪ እንዳይዳረግ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ ለተጠቀሱት ግዥዎች ዋጋው የወቅቱ የገበያ ዋጋ መሆኑ በገበያ ጥናት ባለሙያዎችን በማረጋገጥ ነው የተፈፀመው፡፡

2.14.1 ግኝት፣ የተገዙ ዕቃዎች በናሙናው መሰረት በቴክኒክ ኮሚቴ ያልተረጋገጠ፣

የፌደራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ-12 የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማንኛውንም ስቶክ ሲቀበሉ ማድረግ ያለባቸው በፍደል ለ/ የዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊው የዕቃውን ትክክለኛነት ከተሰጠው ትዕዛዝ የዕቃ ዝርዝር (specification) ጋር በማመሳከር ወይም ባለሙያ የሚፈልግ ከሆነም በባለሙያ ስለትክክለኛነቱ ማረጋገጫ ማግኘት እንዳለበት ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች በቁጥር 2/ ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በተፈላጊ ባህርያት ዝርዝር (specification) መሰረት መቅረቡን ወይም አገልግሎት መስጠቱን፣ በቁጥር 4/ አስፈላጊ ሲሆን ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች የፅሁፍ ማረጋገጫ መቅረብ እንዳለበት መመሪያው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፡-

- በዋና ግቢ የፈርኒቸር ዕቃዎች ግዥ ብር 1,219,273.05፣ የመጋረጃ ግዥ ብር 799,813.27፣ የምንጣፍ ግዥ ብር 237,337.00፣ የፕሪንተር ግዥ ብር

148,439.35፣ የኮምፕዩተር ዕቃዎች ግዥ ብር 109,761.75፣ የታብሌት ግዥ ብር 96,600.00 የፕሪንተር ሄድ ግዥ ብር 89,010.00 የጣት አሻራ ግዥ ብር 80,500.00 የፍሪጅ ግዥ ብር 37,200.00 እና ኤይር ኮመፕሮሰር (Air comproser) ብር 10,580.00 ግዥ የፈጸመ ሲሆን፣ የተገዙ ዕቃዎች በሚፈለገው መሰረት ስለመቅረባቸው በቴክኒክ ኮሚቴ ተረጋግጦ ገቢ መሆን ሲገባው በድምሩ ብር 2,828,514.42 የተገዙ ዕቃዎች በናሙናው መሰረት ገቢ ስለመሆናቸው የቴክኒክ ኮሚቴ ያረጋገጠበት ደብዳቤ ከክፍያ ሰነድ ጋር ያልቀረበ መሆኑን፣

- በኤሌትሪካል ኢንጅነሪንግ ት/ቤት የፈርኒቸር ግዥ ብር 10,909.99፣ የመማር ማስተማር ዕቃዎች ግዥ ብር 119,277.50፣ የእስቴሽነሪ ዕቃዎች ግዥ ብር 167,733.25፣ የመጋረጃ ግዥ ብር 312,014.09፣ የቁልፍ ግዥ ብር 93,955.00 በአጠቃላይ በድምሩ ብር 703,889.83 የተገዙ ዕቃዎች በናሙናው መሰረት ገቢ ስለመሆናቸው የቴክኒክ ኮሚቴ ያረጋገጠበት ደብዳቤ ከክፍያ ሰነድ ጋር ያልቀረበ መሆኑን፣
- የአፕላይድ ተፈጥሮ ሳይንስ ት/ቤት የፈርኒቸር ግዥ ብር 67,261.66፣ የመማር ማስተማር ዕቃዎች ግዥ ብር 658,978.76፣ የጽህፈት መሣሪያዎች ግዥ ብር 87,205.88፣ የመጋረጃ ግዥ ብር 30,636.00፣ የዲቫይደር ግዥ ብር 23,920.00 በድምሩ ብር 868,002.30 የተገዙ ዕቃዎች በናሙናው መሰረት ገቢ ስለመሆናቸው የቴክኒክ ኮሚቴ ያረጋገጠበት ደብዳቤ ከክፍያ ሰነድ ጋር ያልቀረበ ሲሆን፣

በአጠቃላይ ብር **4,400,406.55** የተገዙ ዕቃዎች በናሙናው መሰረት ገቢ ስለመሆናቸው የቴክኒክ ኮሚቴ ያረጋገጠበት ደብዳቤ ከክፍያ ሰነድ ጋር አልቀረበም፡፡

2.14.2 ስጋት፣

ዩኒቨርሲቲው በግዥ የሚመጡ ዕቃዎች በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት በቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ የሚገባ ከሆነ መስሪያ ቤቱ በማይፈልገው መስፈርት ሊገባ ስለሚችል የመንግስት ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ጥራት የሌላቸው ዕቃዎች በማስገባት ማገልገል የሚገባቸውን ጊዜ ሳያገለግሉ ለብልሽትና ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡

2.14.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማናቸውም የዕቃ ግዥም ሆነ የአገልግሎት ግዥ መከናወን ያለበት የመንግስትን ደንብና መመሪያ መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል። ከደንብ እና ከመመሪያ ውጭ የሚከናወን የዕቃም ሆነ የአገልግሎት ግዥ ተቀባይነት እንደሌለው ተውቆ ደንብና መመሪያን መሰረት ያደረገ አሰራር ተግባራዊ ሊሆን ይገባል።

2.14.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ሂሣብ ክፍያ ሲፈጸም አብዛኛው ጊዜ ትኩረት የሚሰጡ የመወዳደሪያ ሠንጠረዥ፣ ሞ/19 የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሲሆን ሞደል 19 ንብረት ክፍል አጣርቶ ገቢ ያደርጋል በሚል ታሳቢ ሲሆን በቴክኒክ ኮሚቴ የተረጋገጠበትን ሰነድ እንዲያያዝ ይደረጋል። ለወደፊቱም እንደማንኛውም የሂሣብ ሰነድ ተሟልቶ እንዲቀርብ በማድረግ የማሻሻያ እርምጃ እንወስዳለን።

2.15.1 ግኝት፣ ሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ክፍያ፣

የፌዴራል መንግስት የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር መመሪያ ግንቦት 1999 ዓ.ም የወጣው የወጪ ሂሳብ መደቦች ወጪ የሚደረግባቸውን የሂሳብ መደቦች መግለጫ በዝርዝር ተቀምጧል። ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲውን የወጪ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲድርግ፡-

- ለማህበራዊ አገልግሎት የሚውል ለምርምር ስራ ብር 161,000.00 በሂሳብ መደብ 6412 መመዝገብ ሲገባው ለተለያዩ ክፍያዎች በሚል በሂሳብ መደብ 6419 ተመዝግቦ የተከፈለ መሆኑን፣
- ለ2009 ዓ.ም ተመራቂ ተማሪዎች የሽልማት ዕቃ ግዥ ብር 128,653.31 በሂሳብ መደብ 6417 መመዘገብ ሲገባው ለተለያዩ ክፍያዎች በሚል በሂሳብ መደብ 6419 ተመዝግቦ የተከፈለ መሆኑን፣
- ለማህበረሰብ አገልግሎት የሚውል የመጸዳጃ ቤት ስራ ብር 125,596.88 በሂሳብ መደብ 6412 መመዝገብ ሲገባው ለተለያዩ ክፍያዎች በሚል በሂሳብ መደብ 6419 ተመዝግቦ የተከፈለ መሆኑን፣
- የዓመት ዕረፍት ክፍያ ብር 78,062.80 በሂሳብ መደብ 6111 መመዝገብ ሲገባው ለሰራተኞች የሚደረጉ ልዩ ልዩ ክፍያዎች በሚል በሂሳብ 6116 ተመዝግቦ የተከፈለ መሆኑን፣

- ለመምህራን የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 70,692.00 ለሰራተኞች የሚደረጉ ልዩ ልዩ ክፍያዎች በሚል በሂሳብ 6116 መመዝገብ ሲገባው ለምግብ በሚል በሂሳብ መደብ 6216 ተመዝግቦ የተከፈለ መሆኑን፣
- የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 434,956.00 ለሰራተኞች የሚደረጉ ልዩ ልዩ ክፍያዎች በሚል በሂሳብ 6116 መመዝገብ ሲገባው ለውሎ አበል በሚል በሂሳብ መደብ 6231 ተመዝግቦ የተከፈለ መሆኑን፣
- የነዳጅ ኩፖን ግዢ ብር 400,384.00 ነዳጅና ቅባት በሚል በሂሳብ 6217 መመዝገብ ሲገባው ለአላቂ የቢሮ ዕቃዎች በሚል በሂሳብ መደብ 6212 ተመዝግቦ የተከፈለ መሆኑ፤
- የመጽሐፍት ግዥ ብር 799,931.10 ለትምህርት የሚያገለግሉ የትምህርት መሳሪያዎችና አቅርቦቶች በሚል በሂሳብ 6215 መመዝገብ ሲገባው በቋሚ ዕቃ በሂሳብ መደብ 6313 ተመዝግቦ የተከፈለ መሆኑን፣
- የምግብ ግብዓት ግዥ ብር 594,740.00 ምግብ በሚል በሂሳብ መደብ 6216 መመዝገብ ሲገባው ለህትመት በሚል በሂሳብ መደብ 6213 ተመዝግቦ የተከፈለ መሆኑን፣
- የነዳጅ ኩፖን ግዥ ብር 400,384.00 ነዳጅና ቅባት በሚል በሂሳብ መደብ 6217 መመዝገብ ሲገባው ለሕንጻ እድሳትና ጥገና በሚል በሂሳብ መደብ 6244 ተመዝግቦ የተከፈለ ሲሆን፣

በአጠቃላይ ብር **3,194,400.09** ሂሳብ መደቡን ባልጠበቀ ሁኔታ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

2.15.2 <u>ስጋት፣</u>

የፌዴራላዊ መንገግስት የሂሳብ አወቃቃር ስርአት ተግባራዊ ካለመሆኑ በተጨማሪ የበጀት መዛባት ሊያስከትል ይችላል፡፡

2.15.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንገግስት የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር ስርዓት መሰረት ባደረገ አሰራር ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ስለዚህ ለወደፊት የሥራ ክፍሉ ትኩረት ሰጥቶበት ስህተቱ እንዳይደገም ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አለበት፡፡

2.15.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ብር 1,058,575 የአንቲ ቫይረስ ግዥ በ6313 ያልተመዘገቡበት ምክንያት አንቲ ቫይረሱ ዕቃ ስለአልሆነ ሶፍትዌር የተገዛ ስለሆነ የወጪ ሂሣብ ኮድ በግልጽ የማይታወቁ የተለያዩ ወጪ በ6419 (በልዩ ልዩ) መመዝገቡ ትክክል ሊሆን ይችላል፡፡ ለማህበረሰብ አገልግሎትና

ለተማሪዎች የሽልማት ዕቃ ለተለያዩ ወጪዎች ክፍያ በ6419 መመዝገቡ ተገቢ ሊሆን ይችላል፡፡ በ6116 የተመዘገበው ደመወዝ ሳይሆን ለሠራተኛ የሚከፈል ልዩ ልዩ ክፍያ ስለሆነ የሠራተኛ የዓመት ፈቃደ ክፍያ በ6116 መያዙ አግባብ በመሆኑ ትክክለኛ ምዝገባ ነው የሚል አስተያየት አለን፡፡ በሂሣብ ምዝገባ ወቅት የኮዶች መቀያየር በተፈጠረው የሂሣብ ምዝገባ ጥንቃቄ ጉድለት ሊሆን ይችላል፡፡ የመጽሐፍት ግዥን አስመልክቶ ትልልቅ ዋጋ ያላቸው መጽሐፍት ግዥ ሲፈጸም በ6313 መመዝገብ ስለማይቻል የመጽሐፍ ግዥን ከ6215 እንዲመዘገብ ተደርጓል፡፡ የነዳጅ ኩፖን ግዥ በተራ ቁጥር 9 ላይ የተጠቀሰው ግን ሂሣብ ምዝገባው በ6244 ሳይሆን በ6241 ላይ የተመዘገበ ሲሆን ይህም በ6217 መመዝገብ የነበረበት በመኪና ጥገና ላይ መመዝገቡ አግባብ እንዳልሆነ አይተናል፡፡ የሂሣብ ምዝገባን አስመልክቶ ለወደፊቱ ተገቢው ጥንቃሴ ቢደረግ የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

2.16.1 <u>ግኝት፣ ያለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፣</u>

የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል መመሪያ ሰኔ/2004 ዓ.ም የመንግስት ሰራተኞች የሀገር ውስጥ የቀን የውሎ አበል ክፍያ አፈጻጸም አንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 1 ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ለስራ ጉዳይ ከመደበኛው የስራ ቦታው ውጭ ሌላ ስራ ሲያከናውን በዋለበት የክልል ዞን ወይም ወረዳ ከተማ እንዲከፈል ያዛል፡፡ በዚህ አንቀፅ ስር በፊደል (ለ) ሄዶ ዕለቱን ከስድስት ሰዓት ተኩል በኃላ የሚመለስ ከሆነ ለምሳ እንደሚታሰብለት መመሪያው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፤

- ሀምሌ 1 ቀን 2009 ዓ.ም. ላስመረቃቸው ተማሪዎች የሙዚቃ ባንድ ከባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ለተጋበዙ ለ111 ሰዎች ለእያንዳንደቸው የ10 ቀን የዉሎ አበል በመክፈል በድምሩ ብር 172,070.30 ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣
- ከ25/11/08 - 26/11/2008 ዓ.ም ለሁለት ቀን በቢሾፍቱ ከተማ ስልጠና የተሳተፉ ሰራተኞች ለእያንዳንዱ ሰልጠኝ ከአምስት እስከ ሰባት ቀን የውሎ አበል በመክፈል በድምሩ ብር 155,774.00 ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣
- ከአይ-ካፒታል አፍሪካ ኢንሲቲትዩት ጋር በመሆን ሁለተኛውን የምስራቅ አፍሪካ ስሚንቶ ኮንክሪትና ሀይል ሰሚት(2nd East Africa cement concrete& Energy summit) በሚል ከሚያዝያ 11-12/2009 ዓ.ም ለሁለት ቀን በተሰጠው ስልጠና ለተሳተፉት መምህራን እና አስተዳደር ሰራተኞች በተሳተፉት የቀን ብዛት ክፍያ ማከናወን ሲገባው፣ ለእያንዳንዱ ሰልጣኝ ከአምስት እስከ አስር ቀን የውሎ አበል

በመክፈል በድምሩ ብር 62,970.00 ክፍያ የፈጸመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝር ሁኔታው እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ተ.ቁ	የቀን ዉሎ አበልመጠን	መክፈል የነበረበት			ተከፍሎ የተገኘ	ልዩነት በብልጫ የተከፈለ
		የቀን ብዛት	የሰዉ ብዛት	የብር መጠን		
1	193	1	8	193*3*8=4,632	193*10*8=15,440	13,896.00
2	159	1	82	159*3*82=39,114	159*10*82=130,380	117,342.00
3	125	1	21	125*3*21=7,875	125*10*21=26,250	23,625.00
1	171	4	153	171*4*153=104,652	171*7*37=44,289 171*5*105=89,775	81,738.00
2	123	4	15	123*4*15=7,380	147*7*4=4116 147*5*6=4410	7,269.00
3	147	4	10	147*4*10=5,880	123*7*4=3,444 123*5*11=6765	4,836.00
4	595	4	1	595*1*5=2,975.00	595*4*1=2,380	1,785.00
1	206	5	32	32*206*4=26,368.0	32*206*5=32,960.0	6,592.00
2	50	5	4	4*50*4=8,00.00	4*50*5=1,000.00	200.00
3	165	5	4	4*165*4=2,640.00	4*165*5=3,300.00	660.00
4	124	5	7	7*124*4=3,472.00	7*124*5=4,340.00	868.00
5	206	10	2	4*206*2=1,648.00	10*206*2=4,120.00	2,472.00
6	575	10	3	4*575*3=6,900.00	10*575*3=17,250.0	10,350
	ድምር			**213,741.00**	**390,814.00**	**177,073.0**

በአጠቃላይ ብር **177,073.00** በመመሪያው መሰረት ክፍያ መከናወን ሲገባው፣ መከፈል ከነበረበት በላይ በልዩነት ውሎ አበል ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

2.16.2 <u>ስጋት፣</u>

የመንግስትን ገንዘብ ከደንብና መመሪያ ውጭ መጠቀም የመንግስትን መመሪያ ከመጣሱም በላይ የመንግስትን ውስን ሀብት ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

2.16.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ከመንግስት የክፍያ መመሪያና ደንብ ውጭ የሚከፈል ማናቸውም ክፍያዎች ተቀባይነት እንደለሌው ታውቆ ከመመሪያ ውጭ ያለአግባብ የተከፈለው ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም መሰል ስህተት እንዳይከሰት ጥንቃቄ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

2.16.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በውሎ አበል አከፋፈል ላይ የተሰጠው አስተያየት ከሰነዱ ተሰርቶ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ ጥረት ይደረጋል፡፡ ያለአግባብ የተከፈለው ሠራተኛ ካለ ሂሳቡ ተሰልቶ እንዲተካ ይደረጋል፡፡ ሌላው ከታሪፍ በላይ የተከፈለው ሰራተኛ ከተከፈለበት ሰነድ አጣርተን ያለአግባብ ከተከፈላቸው ተመላሽ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በቀን 575 ብር የተከፈላቸው ሠራተኞች /ኃላፊዎች፣ ለተለያዩ መ/ቤቶች የመጡ ከፍተኛ ኃላፊዎችና የበላይ ኃላፊዎች በተቀመጠው የኃላፊዎች አበል ታሪፍ መሠረት የተከፈላቸው ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ስለ አበለ አከፋፈል አስመልክቶ ለወደፊቱ ተገቢው ጥንቃቄ ይደረጋል፡፡

3. የተሰብሳቢ ሂሳብ፣

3.1 ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት ሂሳብ አያያዝ እና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 የሂሳብ አያያዝ አፈፃፀም ንዑስ አንቀጽ 4 የተሰብሳቢ ሂሳብ አያያዝ በፊደል (መ) ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲውን የ2009 በጀት ዓመት የፋይናንስ አፈፃፀም ስርዓት ኦዲት ሲደረግ፣ ከተለያዩ ግለሰቦች እና ድርጅቶች የሚሰበሰብ የመንግስት ገንዘብ በተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታዩ ሂሳቦች መወራረድ ባለባቸው ወቅት መወራረድ ሲገባው፣

- የመንግስት ሰራተኞች ቅድሚያ ክፍያ /Advance to staff 4203/ ይህ መለያ ቁጥር በባለበጀት መስሪያ ቤት ሠራተኞች የሚፈለግ ሲሆን፣ ብር 1,758,597.43 ለጥናትና ምርምር እና ለተለያየ ሥራ ከ2003 ዓ.ም እስከ 2009 ዓ.ም ለበርካታ ሰራተኞች የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በወቅቱ መወራረድ ሲገባው እስከ ሰኔ 30/2009 ያልተወራረደ መሆኑን፣
- ለማህበራዊ ዘርፍ ልማት ኘሮግራም ቅድሚያ ክፍያ /Advance for SSDP 4204/ ይህ መለያ ቁጥር በካፒታል በጀት ውስጥ ለማህበራዊ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ወጪ እንድውል ከተያዘው በጀት ላይ በባለበጀት መስሪያ ቤት

በገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የሚሰጥ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ሲሆን፣ ዩኒቨርሲቲው ለጥናትና ምርምር ሥራ ከ2003 ዓ.ም እስከ 2009 ዓ.ም ለበርካታ ሰራተኞች ብር 5,762,916.54 የተሰጠ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በወቅቱ መወራረድ ሲገባው እስከ ሰኔ 30/2009 ያልተወራረደ መሆኑን፣

- በመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ ሌሎች ቅድሚያ ክፍያ/other Advance with gov.t4210/ይህ መለያ ቁጥር በሁለት በባለበጀት መ/ቤቶች ወይም በባለበጀት መ/ቤቶች እና በክልል መካከል የሚፈጸመው የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 10,000,000.00 በ2009 ዓ.ም የተሰጠ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/2009 ያልተወራረደ መሆኑን፣
- የግዥ ቅድሚያ ክፍያ /purchase Advance 4211 /ይህ መለያ ቁጥር ለግዥ ሰሰራተኞች የሚሰጥ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ሲሆን በመንግስት መመሪያ መሰረት መወራረድ ያለበት ሰባት የስራ ቀናት መብለጥ እንዳለበት መመሪያው ቢያዝም ከ2007 ዓ.ም እስከ 2009 ዓ.ም ለግዥ ሰራተኞች የተሰጠ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ብር 173,810.04 እስከ ሰኔ 30/2009 ያልተወራረደ መሆኑን፣
- ለዕቃ አቅራቢዎች የሚፈጸም የቅድሚያ ክፍያ /Advance to suppliers 4253/ ይህ የሂሳብ መደብ ለአቅራቢዎች የሚሰጥ ቅድሚያ ክፍያ ሲሆን፣ በመንግስት መመሪያ መሰረት ሂሳቡ ከ30 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሊወራረድ የሚገበው ቢሆንም ብር 10,484,316.98 ከ2006 ዓ.ም እስከ 2008 ዓ.ም(በ2009 ዓ.ም. ብር 7,813,118.93 ሳይጨምር) የተከፈተ የሌተር ኦፍ ክሬዲት ሲሆን ብር 6,599,137.91 ከ2004 ዓም እስከ 2009 ዓ.ም ለአቅራቢዎች የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በድምሩ ብር 17,083,454.89 በወቅቱ መወራረድ ሲገባው እስከ ሰኔ 30/2009 ያልተወራረደ መሆኑን፣

በአጠቃላይ ብር 34,778,778.90 ከ2003 ዓ.ም እስከ 2009 ዓም በተሰብሳቢነት የተየዙ ሂሳቦች በወቅቱ መወራረድ ሲገባው እስከ ሰኔ 30/2009 ሳይወራረድ መገኘቱን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል።

3.2 ስጋት፣

የመንግስት ገንዘብ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ በደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ ተሰብሲቦ ገቢ ካልተደረገ የመንግስት የበጀት አሸፋፈን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማድረሱም በተጨማሪ ከቆይታ ብዛት ወደ ማይሰበሰቡበት ደረጃ ሊደርሱ ይችላሉ።

3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማናቸውም ተሰብሳቢ ሂሳብ በመንግስት መመሪያና ደንብ መሰረት ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡ በተጨማሪም በግለሰቦች እና በድርጅቶች እጅ የሚገኝ ተሰበሳቢ ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በ4203 የተለያዩ የመ/ቤቱ ሠራተኞች ለውጪ ሃገር ጉዞ፣ ለጥናትና ምርምር ወጪ አድርገው በበጀት ዓመቱ ያልተወራረደ ሲሆን በተለይ በት/ትና ለላቦራቶሪ ምርምር ሥራ ወደ ውጪ ሃገር የሚሄዱና የፒኤችዲ ባይ ሪሰርች ተማሪዎች የጥናትና መርምር ሥራ ባህሪ ቶሎ የማያልቅና በሃገር ውስጥና በውጪ ሃገር ስለሚሄዱ በበጀት ዓመት ማወራረድ ያልቻሉ ቢሆንም በዚህ ዓመት በጀት ብር 245854.20 ያህል ተወራርዷል፡፡ በ4204 የወጪ ሂሳብ መደብ የታየው ተሰብሳቢ በ2009 በጀት ዓመት ለምርምር ሥራ በቅድሚያ የተከፈላቸው ሲሆን የመርምር ፕሮጀክታቸው ከግማሽ ዓመትና ከአንድ ዓመት በላይ ጊዜ ሊወስድ ስለሚችል ሳይወራረድ ወደ 2010 በጀት ዓመት ቢተላለፍም ከሐምሌ 2009 እስካሁን ብር 2,954,524.00 የተወራረደ ሲሆን ቀሪውም በዚህ ዓመት በጀት ይሰበሰባል (ይወራረዳል) ለዚህም ከሚመለከተው የሥራ ክፍል ጋር ትክክል እየተደረገ ይገኛል፡፡ በወጪ ሂሳብ መደብ 4210 የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከሁለት ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በጋራ የሚያገለግል የኔትወርክ ዕቃ ለመግዛት በማሰብ 10,000,000 ብር በቅድሚያ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የተከፈለ ሲሆን የግዥ ሂደቱ ሲያልቅ ሂሣቡ በወጪ የሚመዘገብ ይሆናል፡፡ 4211 በግዥ ሠራተኞች ላይ የታየው ያልተወራረደ ሂሣብ ሲሆን ግዥ ሠራተኛ በተለያየ ምክንያት ሳያወራርዱ ቢቆዩም እስከ አሁን 2,483.28 በጥሬ ገንዘብ ገቢ አድርጓል፡፡ ብሩም ተመላሽ የተደረገ ሲሆን ቀሪው በህግና ክትትልና ሰነድ በማጣራት ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በወጪ ሂሣብ መደብ 4251 ለሥራ ተቋራጮች ከተከፈለው ቅድሚያ ክፍያ የግንባታ ሂደቱ ያልተጠናቀቀ ስለሆነ ተሰብሳቢ ሂሣብ ክፍያ ሰኔ 30/2009 48,309,956.93 ቢታይም በአሁኑ ጊዜ ብር 18,250,796.58 ተሰብስቦ ቀሪው ብር 35,543,110.14 በቅርብ ጊዜ የሚሰበሰብ ይሆናል፡፡ ተደረጓል፡፡ ለዕቃ አቅራቢዎች ከተከፈለው ቅድሚያ ክፍያ ላይ LC ሲከፈት በወጪ ሂሣብ መደብ 4253 በመያዙ በአሁኑ ጊዜ የ18,990,344.23 ዕቃ ገቢ ሆኖ የርክክብ ሂደት ላይ ስለሚገኝ በቅርብ ጊዜ በወጪ ይመዘገባል፡፡ ቀሪው ከትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

4. የተከፋይ ሂሳብ፣

4.1 ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት ሂሳብ አያያዝ እና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 የሂሳብ አያያዝ አፈፃፀም ንዑስ አንቀጽ 5 ሀ.ማናቸውም ወደፊት ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንዳለበት ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲውን የ2009 በጀት ዓመት የፋይናንስ አፈፃፀም ስርዓት የተለያዩ ተከፋይ ሂሳቦች ለባለመብቱ አካል ተከፍሎ በወቅቱ ሂሳቡ መወራረድ ሲገባው፣

- ልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳቦች /sundry creditors 5002/ ይህ መለያ ቁጥር ከችሮታ ጊዜ ተከፋይ ሂሳቦች በስተቀር ሌሎች ማናቸውም ተከፋይ ሂሳብ ሲሆን፣ ለተለያዩ ድርጅቶችና ግለሰቦች የሚከፈል ሂሳብ ብር 68,875.26 ከ 2007 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2009 ዓ.ም በዕዳነት የተየዘ ሂሳብ በወቅቱ ተከፍሎ መወራረድ የሚገባው ተከፋይ ሂሳቦች ሳይወራረድ መገኘቱን ተረጋግጧል፡፡

4.2 ስጋት፣

የተከፋይ ሂሳብ ለባለመብቱ ድርጅት፤ መ/ቤት ወይም ግለሰብ በወቅቱ አለመተላለፉ ገንዘቡ ለታቀደለት ዓላማ እንዳይውልና በበጀት አጠቃቀም ላይ ተጽዕኖ ሊያሳደር ይችላል፡፡

4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው ማናቸውም ተከፋይ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ማወራረድ አለበት፡፡ ከሰራተኞች የሰበሰበውን የስራ ግብር ለግብር ሰብሰቢው ባለስልጣን ገቢ ሊያደርግ ይገባል፡፡

4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በፍርድ ቤት ትእዛዝና ከተለያዩ ሠራተኞች የወር ደመወዝ ተቀንሶ ለባለመብቱ መላክ የሚቻለው በሚቀጥለው ወር ስለሚሆን በ5002 የተለያየ ተከፋይ ሂሣብ ተጣርቶ ከሐምሌ 2009 እስከአሁን ብር 30,336.38 ለባለመብቱ እንዲከፈል የተደረገ ሲሆን ቀሪውም ባለመብቱ የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብ የሚከፈለው ይሆናል፡፡

5. በጀት፣

5.1 ግኝት፣

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል

ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001 ክፍል 6 የመንግስት ገንዘብ ክፍያ አንቀጽ 30 በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 እስከ 26 በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ በበጀት አዋጁ ለተመለከተው የመንግስት መሥሪያ ቤት እንዲከፈል በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ክፍያ መፈጸም እንደማይቻል ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ለዩኒቨርሲቲው ለ2009 በጀት ዓመት ከተፈቀደው እና ማስተካከያ ከተደረገለት በኋላ የ12 ወር የፋይናንስ አፈፃፀም ኦዲት ሲደረግ፣

- በልዩ ልዩ የወጪ ሂሳብ መደቦች ውስጥ ያልተሰራበት ከመደበኛ በጀት ብር **166,180,563.72** እና ከካፒታል በጀት ብር **181,300,933.51** በአጠቃላይ ብር **347,481,497.23** ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑን፣
- እንዲሁም ዩኒቨርሲቲው ለመደበኛ በጀት ብር 776,111.60 ከተፈቀደው በጀት በላይ የተጠቀመ መሆኑን፣

ተረጋግጧል፡፡

5.2 ስጋት፣

ዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የተፈቀደለት በጀት በአግባቡ አለመጠቀሙ ሊደርስበት ካቀደው ግብ እንዳይደርስ ከማድረጉም በተጨማሪ የሀገሪቱን ውስን ሃብት ያለጥቅም እንዲቀመጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ከበጀት በላይ መጠቀም የህግ ጥሰት ሊያስከትል ይችላል፡፡

5.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ያልተሰራበትን በጀት በተመለከተ ዩኒቨርሲቲው በተጨባጭ ሊሰራ ካቀደው ተግባር ጋር በማገናዘብ እና አፈፃፀሙን በመገምገም የበጀት ዝግጅቱ የሚሻሻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት፡፡ ከበጀት በላይ ስራ ላይ ማዋል አግባብነት ስለሌለው የበጀት ፍላጎቶችን መታየት ያለበት በጀቱ ጥናትንና ዕቅድን መሰረት ያደረገ እና የፋይናንስ ፍላጎትና አፈፃፀም መሰረት በማድረግ ከፍተኛ የወጪ እንቅስቃሴ የሚታይበት ሂሳብ መደቦች ላይ ትኩረት ሊደረግ ይገባል፡፡ ከወዲሁም የበጀት አፈጻጸሙን በማየት በደንቡ መሠረት ዝውውር በማድረግ ሥራ ላይ ሊያውል ስለሚገባ ለወደፊቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

5.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

አብዛኛውን በመደበኛና በካፒታል በጀት ላይ ከተያዘው በጀት ሥራ ላይ ሳይውል የቀረው ከግዥ እና ከግንባታ ሥራዎች ጋር የተያያዘ ሲሆን ግዥን አስመልክቶ ለመማር ማስተማርና ለጥናትና ምርምር ሥራዎች የሚውል የላቦራቶሪ ዕቃዎች ግዥ የጨረታ ሂደት ላይ የነበረና

በበጀት ዓመቱ የጨረታ ሂደቱ አልቆ ክፍያ ለመፈጸም የተወሰኑት በቅድሚያ ክፍያ ደረጃ ላይ የነበሩ በመሆኑ ሲሆን፣ የግንባታ በጀትን አስመልክቶ የተጀመሩ የግንባታ ሥራዎች ወቅቱን ጠብቆ የክፍያ ጥያቂ ባለመቅረቡ የተፈቀደው በጀት በበጀት ዓመቱ ሥራ ላይ ሳይውል ቀርቷል፡፡ በተለያዩ ምክንያት ሥራ ላይ ያልዋለው በጀት ዓመቱ ከማለቁ በፊት ለግንዘብና ኢኮ/ትብብር ሚ/ር አሳውቀን ለሌላ መ/ቤት እንዲዛወር ተደርጓል፡፡በ2010 በጀት ዓመት ተገቢ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡ ከበጀት በላይ አጠቃቀም አስመልከቶ በሂሣብ መደብ 6258 ከበጀት በላይ የተጠቀምንበት ምክንያት የሥልክ አገልግሎት የኢንተርኔት /ብሮድባንድ/ ክፍያ ከኢ/ቴሌኮም ቢል ሲላክልን ውዝፍ ሂሣብ ጭምር በዓመቱ የመጨረሻ ቀናት የከፍያ ቢል ስለአቀረቡልን ለኢ/ቴሌኮም የተከፈለ ስለሆነ ነው፡፡

6. ንብረት፣

6.1 ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 5 የመመሪያው አላማ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፤ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዳለበት ያዛል፡፡ በተጨማሪም በፌደራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 8/2003 በስራ ክፍሎችና ሠራተኞች መካከል ሊኖር የሚገባውን መዋቅራዊ ግንኙነቶች በመመስረተ ሊነጣጠሉ የሚገባቸውን ስራዎችና ኃላፊነቶች በተለያዩ ሰዎች ተከፋፍለው እና ተለይተው እንዲሰሩ የሚያስችል ስልት ዘርግቶ ተግባራዊ መድረግ እንዳለበት ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርስቲው፡-

- የተሽከርካሪ የመለዋወጫ ዕቃዎች ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ እንዲሁም የንብረት ወጪ የሚሰራ በአንድ ሰዉ መሆኑን፣
- የሚወገዱ የተለያዩ የመኪና ጎማዎች ብዛት 250፣ የመኪና ባትሪዎች ብዛት 83፣ ከመነዳሪያ ብዛት 80፣ ፍላፓ በቁጥር 150 እና የተለያዩ አሮጌ ሞተር ሳይክሎች በቁጥር 6 የሚሆኑ መወገድ ሲገባ ንብረት ክፍል ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑን፣
- አገልግሎት የማይሰጡ ወይም በብልሽት ምክንያት የቆሙ ተሽርከሪዎች ተጠግነው አገልግሎት የሚሰጡ ከሆነ ተጣርተው መጠገን ሲገባው ወይም መወገድ ካለባቸው ሳይወገዱ ሰሌዳ ቁጥር 4-03511 ቶዮታ ፒካፕ፣ ሰሌዳ ቁ 4-07079 IVCO፣ ሰሌዳ ቁጥር 4-01232 ቶዮታ፣ ሰሌደ ቁጥር 4-03515 ቶዮታ እና 4-01698 ኒሳን ፒካፕ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ያለአገልግሎት የቆሙ መሆኑን፣

- በዓለም አቀፍ ጨረታ የተገዙ ብዛት ያላቸው የቅየሳ (ሰርቬይንግ) መሳሪያዎች የተቀመጠውን የናሙና መስፈርት ባለማሟላታቸው በሚል ጉዳዩ ተጣርቶ የቴክኒክ መስፈርቱን ካላሟላ ለአቅራቢው ተመላሽ ማድረግ ወይም የናሙናው ትክክለኝነት ተጣርቶ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ሆኖ አገልግሎት መስጠት ሲገባው ከሁለት ዓመት በላይ ሞ/19 ሳይቆረጥለት በቋሚ ንብረት ክፍል ውስጥ ያለ አገልግሎት የሚቀመጥ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡ የ2009 በጀት ዓመት ንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም የቆጠራ ውጤት ሪፖርት ተጠናቆ ያልቀረበ መሆኑን፣
- በ2008 በጀት ዓመቱ የተገዙ የተለያዩ የአላቂ ዕቃዎች በወቅቱ ለተጠቃሚዎች ተሰጥተው አገልግሎት ላይ መዋል ሲገባው በዋና ንብረት ክፍልና በሚኒ ንብረት ክፍል ውስጥ ጥቅም ላይ ሳይውሉ ወደ 2009 በጀት ዓመት የዞሩ ቢሆንም፣ ያለው ስራ ላይ ሳይውል በተጨማሪ ተመሳሳይ ግዥ በመፈጸም ያለአስፈላጊ ወጪ ከማስከተሉም በተጨማሪ የንብረት ክፍል ጥበት ያስከተለ መሆኑን፣
- የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃ እና አላቂ የጽዳት ዕቃ ክፍል ቢን ካርድ፤ ስቶክ ካርድ እና ንብረት ወጪ በአንድ ሰዉ የሚሰራ መሆኑን፣
- የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃ ክፍል ውስጥ አገልግሎት የማይሰጥ ፍሪጅ መወገድ ካለበት ሳይወገድ ወይም ተጠግኖ አገልግሎት መስጠት ሳይችል ከአንድ ዓመት በላይ የተቀመጠ መሆኑን፣
- የውሃና የመብራት የጥገና ግብአቶች ቢን ካርድ እና ስቶር ካርድ የተወሰነ መጠቀም የጀመሩ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ ያልተገባ መሆኑን፣
- የውሃና የመብራት የጥገና ግብአቶች ተለዋዋጭ አላቂ ዕቃዎች ተመላሽ የሚሆኑበት ስርዓት የሌለና ተመላሽ ዕቃዎች ገቢ የማይደረጉ መሆኑን፣
- የእንጨት ምርትና ጥገና ክፍልን ግብአቶች ንብረት የወጪ ሰነድ ሞዴል 22 እንዲሁም እስቶክ ካርድና ቢን ካርድ በአንድ ሰው የሚሰራ መሆኑን፣
- የተበላሹ ግራይንደሮች፣ ድሪሎች፣ ሮተሮች፣ ሳንደሮች እና የብረት መቁረጫዎች ጥገና ሳይደረግላቸው ለረጅም ጊዜ ያለመፍትሄ የተቀመጡ መሆናቸው፡፡
- ከጥቅም ውጭ የሆኑና መወገድ ያለባችው ብዛት ያላቸው የተገነጣጠሉ በሮች፤የተሰባበሩ ሼልፎች እና ብረታ ብረቶች ተከማችተው የእንጨት ምርትና ጥገና ክፍል ፊት ለፊት የሚገኝ መሆኑን፣

ተረጋግጧል፡፡

6.2 ስጋት፣

የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ደካማ በመሆኑ መንግሥት በውስን ሀብት ግዥ የፈፀመው ንብረት ለብክነት የሚያጋልጥ ከመሆኑም በላይ በስራው ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል።

6.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የንብረት ክፍሉን አደረጃጀት በማስተካከል የንብረት መቆጣጠሪያ መዝገቦችንና የቁጥጥር የአሠራር ሥርዓትን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል። በተጨማሪም ዩንቨርስቲው የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ ይኖርበታል።

6.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

- የተሽከርካሪ የመለዋወጫ እቃዎችን ንብረትን ቢን ካርድና ስቶክ ካርድን እንዲሁም ንብረት ወጪ የሚሰራ በአንድ ሰው መሆኑ ለሚለው ጥያቄ ከዚህ በፊትም በገለጽነው መሰረት የሰው ሃብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ነው ይህን መመለስ የሚችለው ምክንያቱም የተዋቀረ የሰው ኃይል መዋቅር በመሆኑ፣
- ያልተወገዱ የመለዋወጫ ዕቃን በተመለከተ ከዚህ በፊት በቀን 09/01/10 በተጻፈው ደብዳቤ መሰረት ለኢፌድሪ ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት እንዲያስወግድልን ጠይቀናል፣
- አገልግሎት የማይሰጡ ወይም በብልሽቱ ምክንያት የቆሙ መወገድ ያለባቸው ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ፡-403511 ዮዮታ ፒካፕ፣ 4-07079 አይቪኮ መኪና፣ 4-01232 ቶዮታ፣ 4-03515 ቶዮታ፣ 4-01698 ኒሳን ፒክ አፕ ተሽከርካሪዎችን ለማስወገድ ዲክላሪስዮን ፍለጋ ከፍተኛ ጥረት ያደረግን ሲሆን የተወሰኑ መኪናዎችን መረጃ ልናገኝ ያልቻልን ሲሆን መረጃ የተሟላላቸውን ለመ/ግ/ን/ማ አገልግሎት የይወገድልን ጥያቄ አቅርበን እንዲወገዱ ጥረት ተደርጓል። ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ 1 ገፅ ኮፒ አባሪ ያደረግን መሆኑን እንገልጻለን።

7. ልዩ ልዩ፣

7.1 እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

- የቤት አበል ላይ የቤት ተመን ዋጋ እየተቀነሰ ልዩነቱ የቤት አበል በሚል በድምሩ 162,650.00 ብር ያላግባብ ተከፈላቸው ተገኝቷል።
- በውጭ ሀገር ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ መምህራን መመለስ በነበረባቸው ሳይመለሱ የቆዩ በድምሩ ብር 40,442.00 ያለአግባብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል።

- በጠቅላላ ብር 1,035,900.00 ዩኒቨርሲቲው በራሱ የክፍያ ስርዓት በማውጣት ከመደበኛ በጀት ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል።
- ዩኒቨርስቲ ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች ለጥናትና ምርምር ማካሄጃ (Msc Thesis) ድጎማ አዲስ የሚገቡ ተማሪዎችን ለመፈተን ወደ ተለያዩ ክልሎች ለተጓዙ መምኅራን የሞያ አበል እና ካሪኩለም ሪቪዉ ወርክ ሾፕ (curriculum review work shop) ላይ ለተሳተፉ በሚል ብር 772,610.00 አላግባብ ከመንግስት መመሪያና ደንብ ውጪ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱን፣
- በድምሩ ብር 1,777,374.15 የተለየያዩ ዕቃዎች በዋጋ ማቅረቢያ የተገዛ መሆኑን፣
- በጠቅላላ የብር 4,209,386.47 በግልፅ በጨረታ መገዛት ሲገባው በቀጥታ የተፈጸመ መሆኑ፣
- የብር 7,296,089.99 ወጪዎች የሂሳብ መደባቸውን መሰረት ያላደረገ መሆኑ፣
- በድምር ብር 913,544.48 በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ክፍያ መፈፀሙ ተረጋግጧል።
- ዩኒቨርሲቲው ለአንድ ኮንትራክተርና ለአንድ አማካሪ ድርጅት በጠቅላላ ብር 28,906,495.29 ከመመሪያው ውጭ ከጠቅላላ ዋጋ ከ30% በላይ ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል።
- በጠቅላላ ብር 39,697,017.64 ባላላቀ ስራ ከውሉ በላይ በብልጫ ተከፈሎ ተገኝቷል።

7.2 ስጋት፣

በኦዲት ሪፖርቱ ላይ እርምጃ ባለመወሰዱ ምክንያት ኦዲተሩ የውስጥ ቁጥጥሩና የአሰራር ስርዓቱ ላይ አሜኔታ እንዳይኖረውና ለተጨማሪ ብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል።,

7.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በዩኒቨርሲቲው የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እንዲቀረፍ ብሎም ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር በኦዲት በሚሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት በአስቸኳይ የእርምት እርምጃ በመውሰድ የበኩሉን አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይገባል።

7.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝት በአብዛኛው በ2009 በጀት ዓመት የተስተካከሉና ቀሪዎቹም ባዘጋጀነው የማስተካከያ መርሃ ግብር መሰረት በዚህ በጀት ዓመት የሚስተካከሉ ይሆናሉ።

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የስራ ትብብር እናመሰግናለን!!!